# ጥበብ፣ ያኔ እና አሁን

የዕብራውያን ጥበብ ብዙዎቹ የአሁኑ ዘመን ክርስቲያኖች ያልለመዱት ዓይነት ሥነ ጽሑፍ ነው። ምንም እንኳ የጥበብ ሥነ ጽሑፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፊ ክፍሎችን ቢሸፍንም፥ ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ በትክክል ባለመረዳት ወይም ከሕይወታቸው ጋር ባለማዛመድ እግዚአብሔር ያሰበላቸውን በረከት ሳያገኙ ይቀራሉ። ይሁንና፥ በአግባቡ ከተረዳንና ከተጠቀምን ጥበብ ለክርስቲያናዊ አኗኗር ጠቃሚ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። አላግባብ ከተጠቀምንበት ደግሞ ለራስ ወዳድነት፥ ለቁሳዊነት፥ አርቆ መመልከት ለጎደለበት ባሕርይ መሠረት ሊጥል ይችላል። ይህም እግዚአብሔር በዚህ የጽሑፍ ዘርፍ ሊያከናውን የፈለገው ተግባር ተገላቢጦሽ ነው።

ሦስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለምዶ «የጥበብ» መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ። እነዚህም መክብብ፥ ምሳሌና ኢዮብ ናቸው። በተጨማሪም፥ በምዕራፍ 11 ውስጥ እንደተመለከትነው በጥበብ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚመደቡ አንዳንድ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎችም አሉ። እንዲሁም፥ በተለምዶ የሰሎሞን መዝሙር በመባል የሚታወቀው መኃልየ መኃልይ አለ። ወረድ ብለን እንደምናብራራው፥ ይህ መጽሐፍ ከጥበብ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ መመደቡ ትክክል ይመስለናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ አሳቦች ሁሉ ስለ ጥበብ ጠንከር ያለ መልእክት የሚያስተላልፉ አይደሉም። ነገር ግን በአጠቃላይ በጥበብ ምድብ ውስጥ የሚገቡ አሳቦችን ይይዛሉ።

## የጥበብ ባሕርይ

«ጥበብ ምንድን ነው?» ለሚለው ጥያቄ የሚከተለውን አጭር ብያኔ እናቀርባለን። ጥበብ በሕይወት መንፈሳዊ ምርጫዎችን ማካሄድ ነው። ይህ ተገቢና ክርስቲያኖችን የማያደናግር አባባል ይመስላል። ችግሩ ግን የብሉይ ኪዳን የጥበብ አሳቦች ሰዎች የማይረዱቸውና የሚያካሄዱቸው ምርጫዎችም መንፈሳዊ ሳይሆኑ መቅረታቸው ነው። ይህ ምዕራፍ ስለ ጥበብ ያለህን ግንዛቤና ተዛምዶ እንድታጠራ ይረዳሃል።

### *የጥበብ ሥነ ጽሑፍን አላግባብ መጠቀም*

በባሕላዊ መልኩ፥ የጥበብ መጻሕፍት በሦስት መንገዶች አላግባብ ከግልጋሎት ላይ ውለዋል።

በመጀመሪያ፥ ብዙውን ጊዜ ሰዎች እነዚህን መጻሕፍት የሚያነቡት በከፊል ነው። በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፈው ደራሲ ሊያስተላልፍ የፈለገው አጠቃላይ መልእክት እንዳለ መገንዘብ ይሳናቸዋል። ከዓውደ ንባባቸው የወጡ ቁርጥራጭ የጥበብ ትምህርቶች ትክክለኛና ተግባራዊ ቢመስሉም፥ አላግባቡ ከሰዎች ሕይወት ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ በመክብብ 3፡2 ለመወለድና ለመሞት ጊዜ እንዳለ የሚናገረው ክፍል በዓውደ ንባቡ ውስጥ ሲታይ የሕይወትን ከንቱነት የሚያመለክት ነው። (ይህም ማለት ሕይወትህ ምንም ያህል መልካም ወይም ጥሩ ቢሆንና ቀንህ ሲደርስ መሞትህ አይቀርም።) ብዙ ክርስቲያኖች ግን ይህ ክፍል እግዚአብሔር የእኛን ዕድሜ መርጦ ይለየዋል የሚል አሳብ አላቸው። ከዓውዱ ሲታይ ግን መክብብ 3፡2 የሚያስተምረው ይህንን አይደለም።

ሁለተኛ፥ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የጥበብ ቃላትንና ምድቦችን፥ እንዲሁም የጥበብ ስልቶችንና ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታዎችን ለመለየት ይቸገራሉ። በመሆኑም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥበብ ዓውዶች ለቀረቡት የተሳሳቱ ፍችዎችን ይሰጣሉ። ለአብነት ያህል መጽሐፈ ምሳሌ 14፡7ን አንብብ። «ከተላላ ሰው ራቅ፤ ከከንፈሮቹ እውቀት አታገኝምና።» ይህ ማለት ክርስቲያኖች ከአእምሮ ዘገምተኞች፥ ካልተማሩት ወይም የአእምሮ ሕመም ካለባቸው ሰዎች ጋር መተባበር የለባቸውም ማለት ነው? በፍጹም አይደለም። መጽሐፈ ምሳሌ «ተላላ» (ሞኝ) ሲል፥ «የማይታመን»፥ ማለትም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን እንደ ራሱ ምኞት የሚኖር፥ ከራሱ በቀር የበላይ ባለሥልጣናትን የማያውቅ ማለቱ ነው። «መራቅ» የሚለው ደግሞ ከዓላማ ጋር የተገናኘ ነው። («አታገኝምና»)፥ በመሆኑም፥ መጽሐፈ ምሳሌ እውቀትን ከፈለግህ ከሞኝ ሰዎች አታገኝም የሚል መልእክት እንደሚያስተላልፍ መገንዘብ ይኖርብናል።

ሦስተኛ፥ ብዙውን ጊዜ ሰዎች የጥበብ ሥነ ጽሑፍን የሙግት ፈለግ መከተል ይሳናቸዋል። ስለሆነም፥ ትክክል እንዳልሆነ የተገለጸውን አሳብ ለመከተል ይሞክራሉ። ኢዮብ 15፡20ን አንብብ። «ክፉ ሰው ዕድሜውን ሙሉ፣ ጨካኙም በተመደበለት ዘመን ሁሉ ይሠቃያል።» ክፉ ሰዎች ደስታን ሊያገኙ አይችሉም የሚለው ይህ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተላለፈ መልእክት ይመስልሃል? ኢዮብ ጠንከር ብሎ ተቃውሞታል። ይህ ጥቅስ የኢዮብ «አጽናኝ» ነኝ የሚለው ኤልፋዝ ይህ ሁሉ ሥቃይ የደረሰበት ክፉ ሰው በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ የገለጸበት የንግግር ክፍል ነው። ወደ በኋላ ላይ በመጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔር የኢዮብን አሳብ አጽድቆ፥ የኤልፋዝን

ያወግዛል። ነገር ግን ጠቅላላውን የአሳብ ፈለግ ካልተከተልህ ይህንን ልታውቅ አትችልም።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናደርገው ነገር ቢኖር የጥበብ ሥነ ጽሑፍ ምን እንደሆነና ምንስ እንዳልሆነ መግለጽና አንዳንድ ጠቃሚ ምልከታዎችን ማካሄድ ይሆናል። እንዴት ልንረዳቸው እንደሚገባን ለማሳየት አንዳንድ የጥበብ መጻሕፍትን በናሙናነት ካቀረብን በኋላ፥ በመጨረሻ እንዴት በትክክል ለመተርጎም እንደሚቻል የሚያግዙትን መመሪያዎች እናቀርባለን። ብዙውን ጊዜ አላግባብ ከግልጋሎት ላይ እንደሚውል ስላመንን፥ ለመጽሐፈ ምሳሌ ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን።

## *ጠቢብ ማን ነው?*

ጥበብ በሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ምርጫዎችን ማድረግ እንደሆነ ከዚህ በላይ ገልጸናል። ይህም ጥበብ ግላዊ ክፍል እንዳለው ያመለክታል። ጥበብ አንድ ሰው ሕይወት የምትጠይቃቸውን ብዙ ምርጫዎች በሚያካሄድበት ጊዜ ከእውነት አንጻር ተግባሩን ሲያከናውንና ሲያስብ የሚገኝ እንጂ፥ ንድፈ አሳባዊና ረቂቅ ነገር አይደለም። ስለሆነም ብሉይ ኪዳን አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች የበለጠ ጥበብ እንዳላቸውና አንዳንዶች ጥበብን ለማግኘት እጅግ በመትጋታቸው «ጠቢባን» (በዕብራይስጥ ሐካም) ተብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ ያስረዳል። ጠቢብ ሰው ተግባራዊ እንጂ ንድፈ አሳባዊ ብቻ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ተገቢዎቹን ዕቅዶች የማውጣት ፍላጎት አለው። እነዚህም በሕይወት ውስጥ የተፈለጉትን ውጤቶች የሚያመጡ ምርጫዎች ናቸው።

ከምርጫዎች ሳቢያ የሕይወታችን ጠቅላላ ግሥጋሤ ሊታይ የሚችልበት እውነተኛ ገጽታ አለ። እንዲያውም የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በተወሰነ ደረጃ የምርጫ ጉዳዮች ናቸው። ጠዋት በስንት ሰዓት ከመኝታችን እንደምንነሣ፥ መጀመሪያ ምን እንደምናደርግ፥ የት እንደምንሠራ፥ ከማን ጋር እንደምንነጋገር፥ እንዴት እንደምንናገር፥ ምን እንደምንፈጽም፥ ነገሮችን መቼ እንደምንጀምርና እንደምናቆም፥ ምን እንደምንበላ፥ ምን እንደምንለብስ፥ ከማን ጋር እንደምንተባበር፥ የት እንደምንሄድ፥ ከማን ጋር እንደምንሄድ ሁሉ እንወስናለን። አንዳንዶች በፍጥነት የሚወሰኑ ሲሆኑ (ለምሳሌ፥ ለምሳ ምን እንደምንበላ)፥ ሌሎች ደግሞ ከረዥም ጊዜ በፊት የተወሰኑና በየዕለቱ መደረግ የሚገባቸው ናቸው። (የት እንደምንኖር፥ ማንን እንደምናገባ፥ ምን ዓይነት ሥራ እንደምንሠራ)፤ አንዳንዶች ደግሞ የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ ምርጫ ውጤቶች ላይሆኑ ይችላሉ (ዘፍጥ. 45፡8)፤ ሌሎች

ደግሞ በከፊል የእኛ ምርጫዎች ይሆናሉ (ምሳሌ 16:33)። ይሁንና፥ ምርጫዎች የሕይወትን አቅጣጫ ያቅዳሉ።

የጥንት ሰዎች ይህንን ያውቁ ስለነበር፥ በእስራኤል ብቻ ሳይሆን በጥንቱ ባሕል ሁሉ ውስጥ የነበረው የጥበብ ሥነ ጽሑፍ የሕይወትን ምርጫዎች እንዴት ከሁሉም በተሻለ መልኩ ማካሄድ እንደሚቻል ለመገምገም እንደሞከሩ እንመለከታለን። እስራኤላውያን ያልሆኑት ሰዎች የጥበብ ግብ ከሁሉም የላቁ ምርጫዎችን ማካሄድ ሲሆን፥ ዓላማውም ምርጥ ሕይወትን ማጣጣም ነበር። በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ እዚህ ላይ የጨመረው አሳብ ቢኖር ጥሩ የሚባሉ ምርጫዎች መንፈሳዊ ምርጫዎች ብቻ እንደሆኑ የሚያስረዳውን ዋንኛ ነጥብ ነበር። ስለሆነም፥ «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» የሚለው የመጽሐፈ ምሳሌ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ እናገኘዋለን። እግዚአብሔርን ካላመንህና ካልታዘዝህ መንፈሳዊ ምርጫዎችን እንዴት ልታካሄድ ትችላለህ? ስለሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብ የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ይህም በረቂቅ ወይም በንድፈ አሳባዊ መልኩ ሳይሆን ሕይወትህን ለእርሱ ማስረከብን የሚጠይቅ ነው። ከዚያ በኋላ፥ አጠቃላይ አቅጣጫህ ትክክል ይሆናል። መንፈሳዊ ምርጫዎችን ለማድረስ ውስን ደንቦችንና አመለካከቶችን በምትማርበት ጊዜ፥ ለጥበብ አኗኗር የሚጠቅም የበለጠ ትክክለኛ የአመራር አቅጣጫ ሊከተልህ ይችላል።

ስለሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው የጥበብ ፍች ከአእምሮ እውቀት ( . .) ጋር የሚገናኝ አይደለም። ምንም እንኳ ከተገለጸው እውነት አንጻር ከተተረጎመ ግላዊ ልምድ ጠቃሚ ትምህርት ቢሆንም፥ ይህ የአገላለጽ ወይም የዕድሜ ብቃት ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም ይህ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብና ከዚያም እርሱን ደስ የምናሰኝበትን ብቃት የማግኘት ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ያዕቆብ 1:5 እግዚአብሔር ጥበብን ለሚጠይቁት እንደሚሰጥ የሚናገረው። ይህም በመጸለያችን የበለጠ አዋቂዎች እንደምንሆን ሳይሆን፥ ይበልጥ መንፈሳውያን እንደምንሆን የሚያመለክት ነው። ያዕቆብ 3:13-18 እግዚአብሔር የሚሰጠውን ጥበብ ከሌሎች እንዴት መቅደም እንደሚቻል ከሚታወቅበት ዓለማዊ ጥበብ በማነጻጸር ያብራራል።

ግቡ ኃላፊነት ያለበትና ስኬታማ አኗኗር ነው እንዲህ ዓይነቱ ጥበብ የሕንጻ ግንባታን ለመሳሰሉት የሙያ ተግባራት (ይህንን በዘጸአት 31:3 «ጠቢብ» ከተባለው የመገናኛው ድንኳን አናጺ ባስልኤል ጋር አነጻጽር) ወይም ለመርከብ ሥራ አገልግሏል (ሕዝ. 27:8-9)። እንዲሁም ደግሞ የሌሎችን ደኅንነት የሚመለከቱ ውሳኔዎችን

የሚያስተላልፉ ሰዎች ጥበብን ይሹ ነበር። እንደ ኢያሱ (ዘዳግ. 34:9)፥ ዳዊት (2ኛ ሳሙ. 14:20)፥ እና ሰሎሞንን (1ኛ ነገ. 3:9፥ 12) የመሳሰሉ የፖለቲካ መሪዎችም አመራራቸው የተሳካ ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ እንደተሰጣቸው ተገልጾአል። የሰው ልብ የጥበብ ምንጭ ተደርጎ ከተገለጸበት ሁኔታ (1ኛ ነገ. 3:9፥ 12) ስለ ጠቢብ ሰዎች ችሎታ ተገልጾልናል። በብሉይ ኪዳን ልብ ሥነ ምግባራዊ፥ የፈቃድና ምሁራዊ ገጽታዎችን ያመለክታል።

ስለሆነም የጥበብ ሥነ ጽሑፍ በሰዎችና በባሕርያቸው፥ መንፈሳዊ ምርጫዎችን በማድረግ ምን ያህል እንደተሳካላቸውና የእግዚአብሔርን እውነት በገጠመኞቻቸው ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚማሩ ወይም እንደማይማሩ በመግለጹ ላይ ያተኩራል። ዋናው ሰዎች ጠቢብ ለመሆን መማራቸው ሳይሆን ጠቢብ ለመሆን መፈለጋቸው ነው። የእግዚአብሔርን እውነት በየዕለቱ ከሕይወቱ ጋር ለማዛመድና ከገጠመኙ ለመማር የሚፈልግ ሰው የኋላ ኋላ ጠቢብ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ጥበብን ለራስ ጥቅም ወይም እግዚአብሔርን ከሁሉም በላይ ለማያስከብር ዓላማ መሻቱ አደገኛ ነው። «በራሳቸው አመለካከት ጥበበኛ ለሆኑ ወዮላቸው!» (ኢሳ. 5:21)። በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ጥበብ ሁልጊዜም ከሰዎች ጥበብ ይልቃል (ኢሳ. 29:13–14)።

### *የጥበብ አስተማሪዎች*

በጥንቷ እስራኤል አንዳንድ ሰዎች ጥበብን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ጥበብን ለሌሎች ለማስተማር ጭምር ይተጉ ነበር። ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች በእስራኤል ውስጥ ከነቢያትና ከካህናት ጋር የሚመሳሰል ስፍራ ቢይዙም፥ «ጠቢባን» በመባል ይታወቁ ነበር (ኤር. 18:18)። እነዚህ ልዩ ጠቢባን እስራኤል በነገሥታት መተዳደር ከጀመረችባቸው ከመጀመሪያዎቹ ጊዜያት አንሥቶ (1000 ዓ.ዓ. አካባቢ፥ ከ1ኛ ሳሙ. 14:2 ጋር አነጻጽር) ጥበባቸውን ለሚፈልጉ ሁሉ የማስተማርና የማማከር አገልግሎት ሲሰጡ ኖረዋል። ከእነዚህም አንዳንዶቹ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነት የብሉይ ኪዳንን ክፍሎች ለመጻፍ ችለዋል። ጠቢባን ከእነርሱ ጥበብን ለሚሹ ሰዎች እንደ ወላጆች እንዳገለገሏቸው እንመለከታለን። እስራኤላውያን ከግብጽ ከመውጣታቸው በፊት እንኳ እግዚአብሔር ዮሴፍን «የፈርዖን አባት» ያደረገው ሲሆን (ዘፍጥ. 45:8)፥ በኋላም ዲቦራ የተባለች ነቢይት በእስራኤል «እናት» ተብላለች (መሳ. 5:7)። ስለሆነም፥ ብዙውን ጊዜ በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ጠቢብ ተማሪውን «ልጄ ሆይ» እያለ ሲጠራ እንመለከታለን። የጥበብ አመለካከቶችና አኗኗሮችን ይማሩላቸው ዘንድ

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ እነዚህ ጠቢባን የሚልኩ ሲሆን፥ ጠቢባኑ ደግሞ እንደ ራሳችው ልጆች አድርገው ያስተምሯቸው ነበር።

*ጥበብ በቤት*

ይህም ሆኖ፥ ሰዎች ጥበብን የሚማሩት ከየትኛውም አካባቢ በላይ በቤት ውስጥ ነበር። ዘመናዊ ወላጆች ልጆቻቸው ትክክለኛ የሕይወት ምርጫዎችን እንዲያደርጉ በሚረዱበት ጊዜ ሳያውቁ ሁሉንም የጥበብ ዓይነቶች በየቀኑ ያስተምሯቸዋል። አንድ ወላጅ፥ «መኪና መንገድ ላይ አትጫወት» ከሚለው አንሥቶ «ብርድ እንዳይመታህ በደንብ ልበስ» እስከሚለው ድረስ የአኗኗር ደንቦችን በሚሰጥበት ጊዜ፥ ጥበብን እያስተማረ ነው ማለት ነው። የትኛውም ወላጅ ልጁ ደስተኛ፥ በራሱ የሚተማመንና ለሌሎች የሚጠቅም እንዲሆን ይፈልጋል። ጥሩ ወላጅ በዚህ አቅጣጫ የልጆቹን ባሕርይ በመቅረጽና እንዴት ያለ ባሕርይ ሊኖራቸው እንደሚገባ በማነጋገር ብዙ ጊዜ ያጠፋል። በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ተግባራዊ ምሳሌ ተሰጥቷል። ነገር ግን ምሳሌ ምክሮቹን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጥበብ ሥር ያኖራል። ይህም የትኛውም ክርስቲያን ወላጅ ሊያደርገው የሚገባው ነው። አንድ ወላጅ ለልጁ የሚሰጠው ምክር በጣም ተግባራዊና ዓለማዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ሊሆን ቢችልም፥ አንድ ሰው ሊያደርግ የሚችለው እጅግ ትልቅ ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንደሆነ ከማስገንዘብ መታቀብ የለበትም።

*ጥበብ በሥራ ባልደረቦች መካከል*

ሰዎች በሕይወት ውስጥ ትክክለኛ ምርጫዎችን ለማድረግ ከሚማሩባቸው መንገዶች አንዱ ውይይትና ክርክር ነው። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ወዳለው ጥበብ የሚደረሰው ሌሎች እንዲያነቡና እንዲያሰላስሉ በሚደረግ ረዥም የአንድ ሰው መልእክት (ለምሳሌ፥ መጽሐፈ መክብብ) ወይም የተለያዩ ሰዎች ስለ ሕይወትና እውነት የየራሳቸውን አመለካከት በሚገልጹበት ውይይት ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፥ መጽሐፈ ኢዮብ)። በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ በሰፊት የሚገኘው የጥበበ ዓይነት ምሳሌያዊ ጥበብ የሚባል ሲሆን፥ በመክብብና በኢዮብ ውስጥ የሚገኘው ደግሞ ምናባዊ ጥበብ ይባላል። በመኃልየ መኃልይ ውስጥ የሚገኘው ስሜታዊ ጥበብ ሊባል ይችላል። እነዚህን ነጥቦች ከታች ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን። ለጊዜው ግን ምናባዊ የተባለው ጥበብ እንኳ ሳይቀር ንድፈ አሳባዊ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊና በገጠመኝ ላይ የተመሠረተ (empirical) መሆኑን መዘንጋት የለብህም።

## *በግጥም የተገለጸ ጥበብ*

በብሉይ ኪዳን ዘመን ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ጥበባቸውን ለማስታወስ የተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾችን በመማሪያነት ተጠቅመዋል። እግዚአብሔርም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን የጥበብ ሥነ ጽሑፎች የገለጸው ሰዎች ሊማሯቸውና ሊያስታውሷቸው በሚችሏቸው መንገዶች ነበር። ቀደም ባሉት ሁለት ምዕራፎች እንደተመለከተው፥ ግጥም በጥንቃቄ በተመረጡ ቃላት፥ ድምፀቶችና ስልታዊ ብቃቶች የታጀበ በመሆኑ ከዝርው ንባብ በላይ ይታወሳል። ለዚህም ነው ግጥም የብሉይ ኪዳን የጥበብ መልእክቶች ማስተላለፊይ ሊሆን የበቃው። መጽሐፈ ምሳሌ፥ መክብብ፥ መጽሐፈ ኢዮብ፥ መኃልየ መኃልይ፥ የጥበብ መዝሙራትና ሌሎችም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ የጥበብ ሥነ ጽሑፎች በአብዛኛው በግጥም የተጻፉ ናቸው። ይኸው የግጥም አጻጻፍ ከተከተላቸው ስልቶች መካከል ደግሞ ተመሳሳይ ትይዩነቶች (ምሳሌ 7፡4)፥ ተቃራኒ ትይዩነቶች (ምሳሌ 10፡1)፥ «መደበኛ» (ምሳሌ 21፡16)፥ ስድር (ምሳሌ 31፡10–31)፥ አቻ (መክ. 3፡1–8)፥ አሐዛዊ ድርደራዎች (ምሳሌ 30፡15–31)፥ እና እጅግ በርካታ ንጽጽሮች (እንደ አነጻጻሪ ዘይቤዎችና ተለዋጭ ዘይቤዎች፥ ለምሳሌ፥ ኢዮብ 32፡19፤ መኃ. 4፡1–6) የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። መደበኛ ምሳሌዎች፥ ስውር መንፈሳዊ መልእክት የሚያስተላልፉ (አለጎሪዎች)፥ እንቆቅልሾችና ሌሎችም ግጥማዊ ቴክኒኮች በጥበብ ጽሑፎች ውስጥ ይገኛሉ።

## *የጥበብ ገደቦች*

በጥንቱ ዓለም ሁሉም ጥበብ መንፈሳዊ ወይም ትክክል እንዳልነበረ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። በጥንቱ የምሥራቅ አካባቢዎች ብዙውን ጊዜ ከቤተ መንግሥት ድጋፍ እየተደረገላቸው የጥበብ ምሳሌዎችንና አሳቦችን የሚሰበስቡ ጠቢባን አስተማሪዎችና ጸሐፍት ይገኙ ነበር። ምንም እንኳ እግዚአብሔርን የጥበብ መጀመሪያ ባያደርጉ (ምሳሌ 2፡5–6) እና የጥበብም ዓላማ እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘቱ ላይ ባያተኩርም (ምሳሌ 3፡7)፥ እነዚህ የምሥራቅ አካባቢዎች ጥበቦች በአብዛኛው የብሉይ ኪዳን የጥበብ ሥነ ጽሑፎችን ይመስላሉ። በተጨማሪም፥ የምሥራቅ አካባቢ ጥበብ የሕይወትን ክፍሎች ሁሉ አይሸፍንም። በጣም ተግባራዊ በመሆኑ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ሥነ መለኮታዊና ታሪካዊ ጉዳዮችን አይዳስሱም። የጥበብ ችሎታ መኖሩ በአግባቡ ከአገልግሎት ላይ ለመዋሉ ዋስትና አይሰጥም። ኢዮናዳብ ለአምኖን ያቀረበው የጥበብ ምክር ለመልካም ዓላማ የተሰጠው አልነበረም (2ኛ ሳሙ. 13፡3)። የሰሎሞን ከፍተኛ ጥበብ (1ኛ ነገ. 3፡12፤ 4፡29–34) ብልጽግናና ኃይል እንዲያገኝ

ቢረዳውም፥ ለእግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት ጠብቆ እንዲዘልቅ አላስቻለውም (1ኛ ነገ. 11፡4)። ጥበብ ብሎይ ኪዳን በሚያስተምረው መልክ ግቡን ሊመታ የሚችለው ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚሠራበት ከሆነ ብቻ ነው።

## መክብብ፡ ጭፍግ ጥበብ

መክብብን በተለይ በጥንቃቄ ካነበቡት ክርስቲያኖችን ግራ የሚያጋባ የጥበብ ጽሑፍ ነው። በጥንቃቄ የማያነቡት ሰዎች በችኮላ ለመጠቀም የማንችላቸውን ጥልቅ የሆኑ አሳቦች እንደያዘ አድርገው ሊደመድሙ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነት ሰዎች (መክብብን ትተው) በእነርሱ ግምት በፍጥነት መንፈሳዊ በረከቶችን ሊያስገኙ ወደሚችሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያመራሉ። መክብብን የሚያነቡ ሰዎችም ቢሆኑ ለእግዚአብሔር በታማኝነት የመኖርን ሕይወት በአዎንታዊ መልኩ የሚያበረታታ ስለማይመስል በቅጡ ላይረዱት ይችላሉ። ይልቁንም አብዛኛው የመጽሐፉ ክፍል የሕይወትን ከንቱነት በማሳየትና የኋላ ኋላም ሞት ነገሮችን ዕርቃናቸውን እንደሚያስቀራቸው የሚያስረዳውን የ«ሰባኪውን» ቃል በማስተጋባት፥ ሰው ሁሉ ደስ እንዳሰኘው እንዲኖር የሚመክር ይመስላል። በመሆኑም፥ የሚከተሉትን ዓይነት የመክብብ ምንባቦች የሕይወትን ጭፍግነት የሚሰብኩ ይመስላል።

ሰባኪው፦ «ከንቱ፣ ከንቱ፣

የከንቱ ከንቱ፣

ሁሉም ነገር ከንቱ ነው» ይላል (1፡2)።

ከፀሐይ በታች የተደረገውን ነገር ሁሉ አየሁ፤ ሁሉም ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው (1፡14)።

ከዚያም በልቤ፣ «የሞኙ ዕድል ፈንታ በእኔም ላይ ይደርሳል፤

ታዲያ ጠቢብ በመሆኔ ትርፌ ምንድን ነው?» አልሁ።

በልቤም፣ «ይህም ደግሞ ከንቱ ነው» አልሁ (2፡15)።

የሰው ዕድል ፈንታ እንደ እንስሳት ነው። ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም፤ ሁሉም ከንቱ ነው» (3፡19)።

ሰው እንደመጣ እንዲሁ ይሄዳል፤

የሚደክመው ለነፋስ ስለሆነ፣

ትርፉ ምንድን ነው? (5፡16)።

በምድር ላይ የሚከሰት ሌላም ከንቱ ነገር አለ፤ ጻድቃን ለክፉዎች የሚገባውን፤ ክፉ ሰዎችም ለጻድቃን የሚገባውን ይቀበላሉ፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነገር ነው አልሁ (8፡14)።

እግዚአብሔር ከፀሓይ በታች በሰጠህ በዚህ ትርጉም የለሽ የሕይወት ዘመን ሁሉ--- ከምትወዳት ሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ--- እጅህ የሚያገኘውን ሥራ ሁሉ በሙሉ ኀይልህ ሥራው፤ ልትሄድበት ባለው መቃብር ውስጥ መሥራትም ሆነ ማቀድ፤ ዕውቀትም ሆነ ጥበብ የለምና» (9፡9-10)።

ሰው ምንም ያህል ብዙ ዓመት ቢኖር፤

በእነዚህ ሁሉ ይደሰት፤

ነገር ግን ጨለማዎቹንም ቀናት ያስብ፤

እነርሱ ይበዛሉና፤

የሚመጣውም ነገር ሁሉ ከንቱ ነው (11፡8)።

መክብብ ውስጥ ስለ ሕይወት አሉታዊ አመለካከት ያልያዙ ክፍሎች የሉትም። እስከ መጨረሻው ቁጥር ድረስ ተከታታይ መልእክቱ የሞት መኖር ሕይወትን ከንቱ እንደሚያደርግ ማሳየት ነው። እኛም እንደ ሌሎቹ ሁሉ ነገ ሞተን የምናልፍና የምንዘነጋ ከሆነ፥ የልግስና፥ የምርታማ፥ የመንፈሳዊ ሕይወት መኖሩ ከራስ ወዳድነት፥ የኃጢአትና የችግር ሕይወት ከመኖር በምን ይለያል? ሁሉንም እኩል የሚያደርገው ሞት ሕይወት ሁሉ በእኩል ሁኔታ እንዲያከትም ያደርጋል! ይህ በአሁኑ ዘመን «ህላዊነት» ( እ ስት ንት ል ስም) የተሰኘው የፍልስፍና ዘርፍ የሚያስተምረው አሳብ ሲሆን፥ የሰባኪውም ምክር በይዘቱ ህላዊነት የሰፈነበት ነው። መልእክቱም እግዚአብሔር ከዚህ በላይ የሰጠህ ነገር የለምና እስካለህ ድረስ በሕይወትህ ተደሰት የሚል ነው (8፡15፤ 11፡8-10--- )። ዛሬ የምትችለውን ዓይነት ጥሩ ሕይወት ኑር። ከዚህ በኋላ ምንም ትርጉም የለም። ሰባኪው ጥንቃቄ የታከለበት ንግግር (5፡2-3)፥ ስግብግብነትን ማስወገድ (5፡11-15)፥ በወጣትነት ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት (12፡1-8) ለመሳሰሉት ተግባራዊ የአኗኗር ሁኔታዎች ምክሮችን ይሰጣል።

ነገር ግን ይህ ምክር ዘላለማዊ እሴት የለውም። የተሰጠውም ትርጉም የሌለው ሕይወት ይበልጥ ምቹና ተስማሚ ይሆን ዘንድ ነው። መክብብ ትንሣኤ ሙታንን የሚክድ ሲመስል (2፡16፤ 9፡5)፥ የብሉይ ኪዳንን እምነት ቁልፍ ገጽታዎች ይተቻል (7፡16፤ 5፡1)። ከዚህም በላይ

ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተለዩትን አመለካከቶች ያበረታታል።

ታዲያ ለምንድን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተተው? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። ለዚህ የምንሰጠው መልስ መክብብ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተተው ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያስተምሩትን ለማነጻጸር ነው የሚል ነው። መክብብ 12፡13–14 ይህንኑ ንጽጽር በማቅረብ ለአንባቢው የሚከተለውን አዎንታዊ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

«የነገሩ ሁሉ ድምዳሜ ይህ ነው፤ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትእዛዛቱንም ጠብቅ፤ ይህ የሰው ሁለንተናዊ ተግባሩ ነውና። መልካምም ይሁን ክፉ፣ ስውር የሆነውን ነገር ሁሉ አንድ ሳይቀር፣ ማንኛውንም ሥራ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ ያመጣዋልና።»

ከእነዚህ ሁለት የመጨረሻ ቁጥሮች በስተቀር ጠቅላላው መጽሐፍ እግዚአብሔር ጣልቃ የማይገባበትንና ከሞት በኋላ ሕይወት የሌለበትን ሁኔታ አስመልክቶ ጠንካራ ሙግት ያቀርባል። ስለሆነም ከሞት በኋላ ሕይወት ስለማይታሰብበትና እግዚአብሔር ቢኖርም ከሰዎች ጋር ግንኙነት ስለማያደርግበት አኗኗር መመሪያ ከፈለግህ መጽሐፈ መክብብ ጠቃሚ መረጃ ይሰጥሃል። ሰሎሞን ከእግዚአብሔር ከራቀ በኋላ የጻፈውን «ጥበብ» የሚወክል የሚመስለው (1ኛ ነገ. 11፡1–13) የዚህ መጽሐፍ እውነተኛ ዓላማ እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ሕይወትህን እንደሚያቀዘቅዘው ማሳየት ነው። ይህ አመለካከት እውነት ባለመሆኑ ሊያረካህ አይችልም። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ንድፈ አሳባዊ ሳይሆን ተግባራዊ ክህደት የሚፈጥረው ዓለማዊ ግንዛቤ ነው። አንድ ሰው እግዚአብሔር በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ ጣልቃ እንደማይገባ በሚያስብበት ጊዜ ውጤቱ የመጽሐፈ መክብብን አመለካከት መያዝ ይሆናል። ስለሆነም፥ መጽሐፉ ለጭፍግ ጥበብ የተገላቢጦሽ ሙግት በማካሄድ አንባቢዎቹ «ሰባኪው» በሚሰጠው መልስ ባለመርካት ተጨማሪ ምርምሮችን እንዲያካሄዱ ያበረታታል። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ የሚለው የ12፡13 ምክር ከመጽሐፈ መክብብ ወደ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተለይም እነዚህ ትእዛዛት ወደሚገኙበት ፔንታቱክ (ምዕራፍ 9ን ተመልከት) ያመለክታል።

## ጥበብ በመጽሐፈ ኢዮብ

በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር እውነት በተነጻጻሪነት የቆሙ የተሳሳቱ አሳቦች የሚገኙት በመክብብ ውስጥ ብቻ አይደለም። በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ የኢዮብ ጥሩ ጓደኞች የሆኑት ቢልዳድ፥ ዞፋር፥ ኤልፋዝና ኤሊሁ ብዙ የተሳሳቱ ምክሮችንና የማጠቃለያ

አሳቦችን ሲያቀርቡ እንመለከታለን። መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜ ከፍተኛ መዋቅር ያለው ውይይት እንደሚመስል ትገነዘባለህ። ይህ ውይይት በጣም ጠቃሚ ግብ አለው። ይኸውም በአንድ ሰው ሕይወት የሚፈጸመው ነገር ሁልጊዜም እግዚአብሔር የፈለገው ወይም ትክክል አለመሆኑን ለአንባቢዎች ማስረዳት ነው። በአንድ በኩል፥ ኢዮብ የመከብብን የሚቃረን ዓላማ አለው። በመከብብ ውስጥ የተጠቀሰው ሰባኪ እግዚአብሔር በሰዎች ዕለታዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እንደማይገባ ገልጾአል። በሌላ በኩል፥ የኢዮብ አጽናኞች እግዚአብሔር በየዕለቱ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን፥ በዚህ ሕይወት በሚከሰቱ ነገሮች ፍርዱን እንደሚፈጽም የሚያስረዳ አመለካከት ይዘዋል። መከብብ መጨረሻው ያው ሞት ስለሆነ ምንም ብታደርግ ለውጥ የለውም የሚል አሳብ አለው። የኢዮብ ጓደኞች ግን በዚህ ሕይወት የሚደርስብህ መጥፎም ሆነ ጥሩ እግዚአብሔርን የማስደሰትህ ወይም የማሳዘንህ ውጤት ነው ብለው ይሟገታሉ። ኢዮብ የደረሰበት በሽታ፥ ኀዘን፥ ድህነትና ጉስቁልና የሥራው ውጤት እንዳልሆነ ሲገልጽላቸው እጅግ ተበሳጭተዋል። የጓደኞቹ መልእክት አንድ ሰው ሕይወት ከተሳካለት ይህ ሰውዬው መልካም ለማድረግ የመምረጡ ምልክት እንደሆነና ነገሮች ከተበላሹበት ግን በእግዚአብሔር ኃጢአትን በመሥራት ቅጣት እየደረሰበት መሆኑን የሚያሳይ ነው። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲህ ዓይነት አመለካከት የነበራቸው ሲሆን (ዮሐ. 9፡1-3)፥ ዛሬም ብዙ ክርስቲያኖች ተመሳሳይ አሳብ አላቸው። በመሠረቱ እግዚአብሔር ዓለምን የሚቆጣጠር ከሆነ፥ የሚሆነው ሁሉ እንደ ፈቃዱ የሚወስደው እርምጃ ነው ብሎ ማሰቡ ተገቢ ይመስላል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እንደማያስተምረን መገንዘብ አለብን። ይልቁንም ዓለም የወደቀች፥ በኃጢአት የተበላሸች፥ በሰይጣን አገዛዝ ሥር የምትገኝ (ዮሐ. 12፡31 አንብብ) እና እግዚአብሔር የማይፈልጋቸው ብዙ ነገሮች እንደሚከሰቱ ያስተምሩናል። በተለይም መከራ የግድ የኃጢአት ውጤት ነው ማለት አይቻልም (ሮሜ 8፡18-23 አንብብ)።

መንፈሳዊ ሰው የነበረው ኢዮብ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚጋብዝ ጥፋት እንዳልሠራ ያውቅ ነበር። በንግግሮቹ ሁሉ (ምዕ. 3፥ 6-7፥ 9-10፥ 12-14፥ 16-17፥ 19፥ 21፥ 23-24፥ 26-31) ንጽሕናውንና ያጋጠመውን መከራ አበክሮ ገልጾአል። ለምን እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንዳጋጠሙት ሊገባው አልቻለም። ለጓደኞቹ ግን እንዲህ ዓይነቱ ንግግር ስድብ ነበር። ኃጢአቱን አላምንም በማለቱ እግዚአብሔርን እየተጠራጠረ ነው ብለው ስላሰቡ ሊያሳምኑት ጥረት አድርገዋል። ኃጢአቱን እንዲናዘዝና እግዚአብሔር የእጃችንን የምንቀበልባትን ትክክለኛና ፍትሐዊ ዓለም እንደሚያስተዳድር ለማሳመን ተራ በተራ

ተረባረቡበት። ኢዮብ ግን የሕይወትን ፍትሕ አልበኝነትና አሁን ያለችው ዓለም ልትሆን የሚገባትን ዓይነት እንዳልሆነች አጥብቆ ይሟገታል። በመጨረሻው ላይ ከወይይቱ ውስጥ ራሱን ያስገባው ኤሊሁ፥ እግዚአብሔር ከሰዎች የላቀ እውቀትና መንገዶች እንዳሉት በመግለጽ ተከራከረ። ይህ ማንም ገና ያልዳሰሰውና ለኢዮብ ምላሽ ሊሆን የቀረበ አሳብ ነበር። ኢዮብ ለኤሊሁ ከፊል አርኪና ከፊል አብጋኝ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ለኢዮብና ለሌሎችም መናገር ይጀምራል (ምዕ. 38–41)። እግዚአብሔር ኢዮብን በማረም ነገሮችን ከማስተካከሉም በላይ ከጓደኞች «ጥበብ» ባሻገር ለኢዮብ ፍትሕን ይሰጣል (42፡7–9)። በሕይወት ውስጥ ሁሉም ነገር ፍትሐዊ ነው አይደለም? ለሚለው ጥያቄ ኢዮብ አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል። «ለምን እኔን?» ለሚለው የኢዮብ ጥያቄ ደግሞ እግዚአብሔር ምላሽ ሰጥቷል። መንገዶቹ ከመንገዶቻችን የራቁ ናቸው፤ መከራ አመጣብን ማለት የሚያደርገውን አያውቅም ማለት አይደለም፤ ወይም ደግሞ ይህንን የማድረግ መብቱን የሚቀናቀን አይኖርም። ምርጫዎቹ ሁልጊዜም ከእኛ ምርጫ የላቁ ናቸው።

ይህ በጠራ መልኩ እውነተኛ ጥበብ ነው። የመጽሐፈ ኢዮብ አንባቢ የዓለም ጥበብ ምክንያታዊ ቢመስልም የተሳሳተ መሆኑን፥ የእግዚአብሔር ጥበብ በምን ላይ እንደሚመሠረት፥ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ጽድቅ እንድንታመን የሚያደርገን ምን እንደሆነ ይገነዘባል። ስለሆነም የብሉይ ኪዳንን ምናባዊ ጥበብ ሞዴል ለማስተላለፍ ውይይቱና የታሪኩ መስመር ተጣምረው እንደቀረቡ እንመለከታለን።

## ጥበብ በመጽሐፈ ምሳሌ

መጽሐፈ ምሳሌ ዋንኛ የጥበብ ምንጭ ነው። ይህም ማለት ሰዎች ራሳቸውን ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች ለማድረግና ስኬታማ ሕይወት ለመምራት የሚጠቀሙባቸውን ደንቦችና ሕግጋት የሚሰጥ መጽሐፍ ነው። ምናባዊ ጭፍግነትን ከሚያስተምረው መክብብና ስለዚህች ዓለም ፍትሕ አልበኝነት ምናባዊ ጥበብ ከሚያቀርበው ኢዮብ በተቃራኒ፥ የምሳሌ ጥበብ በአመዛኙ በተግባራዊ አመለካከቶች ላይ ያተኩራል። ጠቅለል ባለ መልኩ መጽሐፈ ምሳሌ «ጊዜ ያለፈባቸው መሠረታዊ እሴቶች» የሚባሉትን ነገሮች እንደሚያስተምር መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ማንም ወላጅ ልጁ ጎዘንተኛ፥ የተከፋ፥ ብቸኛ፥ ገለልተኛ፥ ሕግን ለመጠበቅ የሚቸገር፥ ግብረገባዊነት የጎደለው፥ ችሎታ የሌለው ወይም ድሃ ሆኖ እንዲያድግ አይፈልግም። ወላጅ ማኅበራዊ ተቀባይነትን፥ ከችግር ነፃ መሆንንና ቀጥተኛነትን ጨምሮ ልጆቹ መልካም ሕይወት እንዲኖራቸው መመኘቱ አግባብነት የጎደለው ወይም ስግብግብነት

የኅላበት አስተሳሰብ አይደለም። መጽሐፈ ምሳሌም ይህንኑ እንዲያደርጉ የታሰቡትን ምክሮች የሚለግስ መጽሐፍ ነው። በርግጥ የአንድ ወጣት ሕይወት ሁልጊዜም በመልካም ሁኔታ እንደሚቀጠል ዋስትና ሊኖረን አይችልም። መጽሐፈ ምሳሌ የሚለው ነገሮች ሁሉ እኩል ቢሆኑም፥ አንድ ሰው ኃላፊነት የሚሰማው ሆኖ እንዲያድግ የሚረዱት መሠረታዊ አመለካከቶችና ምሳሌዎች እንዳሉ ነው።

መጽሐፈ ምሳሌ የጥበብንና የሞኝነትን ሕይወት ባለማቋረጥ እያነጻጸረ ያቀርባል። የሞኝነት ሕይወት መለያዎች ምንድን ናቸው? ሞኝነት እንደ ወንጀል (1፡10–19፤ 4፡14–19)፥ በግድየለሽነት ቃል መግባት ወይም ዋስ መሆን (6፡1–5)፥ ስንፍና (6፡7–11)፥ ክፋት (6፡12–15) እና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ቀጥተኛ ሕይወትን የሚጎዳ ወሲባዊ እርኩሰትን የመሳሰሉት ነገሮችን ያካትታል (2፡16–19፤ 5፡3–20፤ 6፡23–35፤ 7፡4–27፤ 9፡13–18፤ 23፡26–28)። በተጨማሪም፥ መጽሐፈ ምሳሌ ለድሆች እንደ ማሰብ (2፡22፥ 27)፥የመንግሥት መሪዎችን እንደ ማክበር (23፡1–3፤ 24፡21–22)፥ ልጆችን የመቅጣት አስፈላጊነት (23፡13–14)፥ ከአልኮል መጠጥ መራቅ (23፡19–21፥ 29–35) እና ወላጅን ማክበር የመሳሰሉትን ነገሮች እንድናደርግ ያበረታታል (23፡22–25)።

በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ብዙ ሃይማኖታዊ አገላለጾችን አናገኝም። እንደ 1፡7፤ 3፡5–12፤ 15፡3፥ 8–9፥ 11፤ 16፡1–9፤ 22፡9፥ 23፤ 24፡18፥ 21 በመሳሰሉት ስፍራዎች የምናገኛቸው ሃይማኖታዊ ቃላትም ቢሆኑ የመጽሐፉን መልእክት በዋንኛነት የሚይዙ አይደሉም። መንፈሳዊ ለመሆን ሁሉንም ነገር የግድ ሃይማኖታዊ ማድረግ አያስፈልግም። እንዲያውም፥ መጽሐፈ ምሳሌ ቁሳዊ፥ ዓለም የሆነ ችግር ያለበት ይመስል ሁሉንም ነገር መንፈሳዊ ለማድረግ የሚወሰደውን እርምጃ ለማረም የሚረዳ መጽሐፍ ነው። ሁሉንም ነገር መንፈሳዊ ለማድረግ የሚሞክሩ ሰዎች እግዚአብሔር መጀመሪያ ዓለምን በፈጠረ ጊዜ «እነሆ፥ መልካም ነው» ሳይሆን «እነሆ፥ መጥፎ ነው» እንዳለ አድርገው የሚያስቡ ይመስላል።

## *መጽሐፈ ምሳሌን እንዴት በአግባቡና አላግባብ መጠቀም እንደሚቻል*

ስለ መጽሐፈ ምሳሌ ልናስብ የሚገባን አንድ መልካም ነገር እነዚህ ምሳሌዎች በዕብራይስጥ ቋንቋ «ሜሻሊም» (ፈሊጣዊ አነጋገሮች፥ ምሳሌዎች ወይም አባባሎች) እንደሚባሉ ነው። ምሳሌ አጭር የእውነታ መገለጫ ነው። እጥረቱ እየጨመረ በሚሄድበት ጊዜ ዓለም አቀፍ ተዛምዶው እየቀነሰ ይሄዳል። ረዥም፥ በሚገባ የተብራሩና

ዝርዝር አባባሎችን መረዳት ብቻ ሳይሆን፥ ማስታወስም እንደሚቸግር ግልጽ ነው። ስለሆነም ምሳሌዎች ማንም ሰው ሊያስታውሳቸው በሚችል መልኩ የተዘጋጁ ናቸው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ብዙዎቹ ምሳሌዎች የሆነ ምት፥ የድምፅ ድግግሞሽ ወይም ለማስታወስ ቀላል የሚያደርጓቸው የቃላት ብቃቶች አሏቸው። እስኪ፥ «እሳት ለፈጀው ምን ይበጀው» እና «ላይንና ለወዳጅ ጥቂት ይበቃዋል» የሚሉትን የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተመልከት። በመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ «ጀ»ን የሚያካትቱ ሁለት ባለ አንድ ቀለም (single-syllable) ቃላት መደጋገማቸው፥ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ ደግሞ ምትና ዜማ መኖሩ ትኩረትን እንዲስቡ ያደርጋቸዋል። እንደሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች በቀላሉ አይዘነጉም። «ለአንድ ተግባር ራስህን በምትሰጥበት ጊዜ ያለህባቸውን ሁኔታዎችና ምርጫዎች ከግምት ውስጥ አስገባ።» «ቀደም ብለው በሚወሰዱበት ጊዜ ዐበይት ችግሮች እንዳይከሰቱ የሚያደርጉ አንዳንድ የማረሚያ እርምጃዎች አሉ።» እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች የተፈለገውን አሳብ በጥሩ ሁኔታ ቢገልጹም፥ የምሳሌያዊ አባባሎቹን ያህል ቀልብ የመሳብ አቅም የላቸውም። በቀላሉ ሊታወሱም አይችሉም። «እሳት ለፈጀው ምን ይበጀው» የሚለው ግን ምሳሌውን በማያውቁት ሰዎች ዘንድ ሌላ ትርጉም ሊሰጠውና ስለ እሳት ቃጠሎ ብቻ እንደሚያወራ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

የዕብራይስጥ ምሳሌዎችም እንደዚሁ ናቸው። በትክክል ልንረዳቸውና ሊያስተላልፉ የሚፈልጉትን አሳብ ልንገነዘብ ይገባል። ስለ እውነት ሁሉንም ነገር የሚያመለክቱ ሳይሆኑ፥ ወደዚያው የሚጠቁሙ ናቸው። ቃል በቃል ከተወሰዱ ብዙውን ጊዜ ትክክለኛ መልእክት አያስተላልፉም። ነገር ግን የተወሰነ ባሕርይ ለመቅረጽ እንደ መመሪያ የሚያገለግሉ ናቸው። ምሳሌ 6፡27−29ን አንብብ።

ለመሆኑ ልብሱ ሳይቃጠል፣

በጉያው እሳት መያዝ የሚችል ሰው አለን?

አንድ ሰው እግሮቹ ሳይቃጠሉ፣

በፍም ላይ መሄድ ይችላልን?

ከሰው ሚስት ጋር የሚተኛም እንዲሁ ነው፤

የሚደርስባትም ከቅጣት አያመልጥም።

አንድ ሰው፥ «የመጨረሻው መስመር ግልጽ አይደለም። አንድ ሰው ፖስታ እየሰጣት ሳለ ድንገት የአንድን ሰው ሚስት ቢነካስ?

ይቀጣል ማለት ነው? አንዳንድ ሰዎች ዝሙት እየፈጸሙ ሳይቀጡ ይኖሩ የለም?» ሊል ይችላል። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ አተረጓጎም ነጥቡን የሳተ ነው። ምሳሌዎች ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በመጠቀሙና በዝርዝር ሳይሆን በጥቅሚ ነገሮችን በመግለጹ ላይ ያተኩራሉ። ከዚህ ምሳሌ መውሰድ የሚገባህ ትምህርት ዝሙትን መፈጸም ልክ በእሳት እንደ መጫወት ነው የሚል መሆን አለበት። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ፥ በዚህ ሕይወትም ይሁን በሚመጣው እንደሚቀጣቸው የታወቀ ነው። በመጨረሻው ዐረፍተ ነገር ውስጥ «መንካት» የሚለው ፀያፍ ቃል ላለመጠቀም የተደረገ መሆኑን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው (1ኛ ቆሮ. 7፡1፤ ምዕራፍ 2ን ተመልከት)። ይህም መንፈስ ቅዱስ እንዲተላለፍ የፈለገውን መልእክት በትክክል እንድንገነዘብ ያስችለናል። ስለሆነም መልእክቱን በትክክል ለማግኘት ከተፈለገ ምሳሌዎችን በጣም ቀጥተኛና ዓለም አቀፋዊ አድርጎ መውሰዱ ትክክል አይሆንም። ለምሳሌ፥ ምሳሌ 9፡13-18ን ተመልከት።

ጥበብ የለሽ ሴት ለፍላፊ ናት፤

እርሷም ስድና ዕውቀት የለሽ ናት።

በቤቷ ደጃፍ ላይ ትሰለታለች፤

በከተማይቱ ከፍተኛ ቦታ በመቀመጫ ላይ ትቀመጣለች።

በዚያ የሚያልፉትን፣

መንገዳቸውን ይዘው የሚሄዱትን ትጣራለች።

እርሷም ማመዛዘን ለጎደላቸው፣

«ማስተዋል የሌላችሁ ሁሉ ወደዚህ ኑ!» ትላለች።

የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል፤

ተሸሽገው የበሉት ምግብ ይጥማል።

እነርሱ ግን ሙታን በዚያ እንዳሉ፣

ተጋባዦችም በሲኦል ጥልቀት ውስጥ እንደ ሆኑ አያውቁም።

ይህም በጥቂት ቃላት ጠቅላላውን አለጎሪያዊ (በንጽጽር ከራሱ ይልቅ ሌላ ታሪክ የሚያመለክት ታሪክ) መልእክት የሚያስተላልፍ በመሆኑ አጭርና የተመጠነ ምሳሌ ነው። የጥበብ አኗኗር ተቃራኒ የሆነው ሞኝነቷ ጋለሞታይቱ በዚያ የሚያልፉትን ወደ ቤቷ ለማስገባት በምታደርገው የመስህብነት ተግባር ተገልጾአል። ሞኙ ሰው

የተከለከለውን ነገር በመፈለጉ ተለይቶ ታውቋል (ቁ.17)። ነገር ግን የሞኝነት ፍጻሜ ረዥም ዕድሜ፥ ስኬት ወይም ደስታ ሳይሆን ሞት እንደሆነም ተገልጾአል። የዚህ አጭር አለኅሪ መልእክት፥ «ከሞኝነት ራቅ!» የሚል ነው። «በሞኝነት አትወሰድ! ሞኝ የሚሳብባቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች (በሌሎች ምሳሌዎች ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የተገለጹትን) ተሻግረህ እለፍ!» ጠቢብ፥ መንፈሳዊ፥ ግብረገባዊ ሰው ከሞኝነት ራስ ወዳድነት የነፃ ሕይወት ይመርጣል። እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎች እውነታቸውን በተምሳሌታዊ መንገድ የሚገልጹ ናቸው።

ሌላው ለውይይታችን የሚጠቅመው ምሳሌ 16፡3 ነው።

የምታደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፤

ዕድሜህም ሁሉ ይሳካልሃል። (በሌሎች ትርጉሞች «ዕቅዶችህ ይሳኩልሃል» ይላል።)

ብዙውን ጊዜ በተሳሳተ መንገድ የምንረዳቸው እንደዚህ ዓይነቶቹን ምሳሌዎች ነው። ምሳሌዎች በፈሊጣዊ መንገድ መልእክቶቻቸውን የሚያስተላልፉ መሆናቸውን ባለመገንዘብ አንድ ሰው ዕቅዶቹን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ከሰጠ የሚፈጸም መሆኑን የሚሳይ መለኮታዊ የተስፋ ቃል ምሳሌ 16፡3 እንደሚናገር ሊያስብ ይችላል። በዚህ ዓይነት መንገድ የሚያስቡ ሰዎች የኋላ ኋላ ማዘናቸው የማይቀር ነው። ሙሉ በሙሉ ራስ ወዳድነት የኅላበትን ዕቅድ ለእግዚአብሔር ሊያቀርቡና በመጠኑ እንኳ የመሳካት አዝማሚያ ካሳየ እግዚአብሔር ባርኮታል ሊሉ ይችላሉ። በችኮላ የሚካሄድ ጋብቻ፥ የቢዝነስ ውሳኔ፥ የሥራ ጉዳይ ሁሉ በቅጡ ሳይታሰብበት ለእግዚአብሔር ይሰጥና ውጤት አልባ ሊሆን ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ለእግዚአብሔር የተሰጠው ዕቅድ አልይዝ ሲል፥ እግዚአብሔር ለምን ቃሉን እንዳልጠበቀ ማሰብ ይከተላል። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሰጠውን ቃሉን ለምን አላከበረም? ነገር ግን ምሳሌ አጠቃላይ እውነት እንጂ ሁልጊዜም የሚፈጸም የማይነቃነቅ የተስፋ ቃል አይደለም። የሚያስተምረውም ለእግዚአብሔር የተሰጠና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተኖረ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር የስኬት ብያኔ የሚሳካ መሆኑን ነው። በዓለም የስኬት ብያኔ መሠረት፥ ውጤቱ የተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል። የኢዮብ ታሪክ ይህንን በሚገባ ያስገነዝበናል።

ስለሆነም፥ እነዚህ ምሳሌዎች አሳብ የሚያቀርቡ የልዩ ምድብ አካላት መሆናቸውን በማጤን ራሳቸው ሊያስተላልፉ ከሚፈልጓቸው መልእክቶች አንጻር ስንረዳቸው ለሕይወታችን ጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

## አንዳንድ ሥነ አፈታታዊ መመሪያዎች

ከዚህ ቀጥለን የምሳሌን ጥበብ ለመረዳት የሚያስችሉ መመሪያዎችን በአጭሩ እናቀርባለን፡-

### *ምሳሌዎች ከእግዚአብሔር የተሰጡን ሕጋዊ ዋስትናዎች አይደሉም*

ምሳሌዎች የተወሰኑ ተግባራዊ ጉዳዮችን የምናከናውንባቸውን የጥበብ መንገዶች ቢያሳዩም፥ መለኮታዊ የስኬት ዋስትናዎች ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም። አንድ ሰው በእነዚህ ቅኔያዊና ፈሊጣዊ የመጽሐፉ ቋንቋዎች የተገለጹትን የጥበብ ምክሮች ከተከተለ በምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሱትን በረከቶች፥ ሽልማቶችና መልካም አጋጣሚዎች ሊያገኝ ይችላል። ነገር ግን መጽሐፈ ምሳሌ አንድ ሰው በየትኛውም ስፍራ ከመቅጽበት ስኬት በስኬት እንደሚሆን አያስተምርም። እግዚአብሔር መጽሐፈ መክብብንና ኢዮብን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያካተተው፥ በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰቱ መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገሮች ከመቅጽበት የሚከሰቱ አለመሆናቸውን ለማሳየት ጭምር መሆን አትዘንጋ። የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንብብ (ምሳሌ 22፡26-27፤ 29፡12፤ 15፡25)።

በዋስትና ቃል እጅ አትምታ፤

ለብድር ተያዥ አትሁን፤

የምትከፍለው ካጣህ፤

የምትተኛበት ዐልጋ ከሥርህ ይወሰድብሃል

(ምሳሌ 22፡26-27)።

ገዥ የሐሰት ወሬ የሚሰማ ከሆነ፤

ሹማምንቱ ሁሉ ክፉዎች ይሆናሉ (ምሳሌ 29፡12)።

እግዚአብሔር የትዕቢተኛን ቤት ያፈርሰዋል፤

የመበለቲቱን ድንበር ግን እንዳይደፈር ይጠብቃል

(ምሳሌ 15፡25)።

ከእነዚህ ምሳሌዎች የመጀመሪያውን (22፡26-27) ከእግዚአብሔር እንደተሰጠ ሁሉን-አቀፍ ትእዛዝ አድርገህ ብትወስድ፥ የባንክ ብድር ላለመውሰድ ስትል ቤት ከመሥራትም ሆነ ከመግዛት ልትታቀብ ትችላለህ። ወይም ደግሞ እንደ ዱቤ (ክሬዲት) ዕዳ ዓይነቱን ባትከፍል የኋላ ኋላ አልጋህን ጨምሮ ሀብትህን ሁሉ እንደምታጣ የሚናገር መስሎ ሊሰማህ ይችላል። በቀጥታ ለመረዳት መፈለግህ ዕዳን መክፈሉ

አቀበት ሊሆን ስለሚችል፥ ስትበደር መጠንቀቅ ይኖርብሃል የሚለውን የምሳሌውን መልእክት እንዳትገነዘብ ያደርግሃል። ምሳሌው ይህንን እውነት ያስቀመጠው አንድን ነገር በቴክኒካዊ መንገድ ሳይሆን ሰፋ ባለ መርህ ለመግለጽ በታቀዱ ጠባብ ቃላት (እጅ መምታት፥ የአልጋ መወሰድ) ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ጻድቅ ሰዎች የዚህን ምሳሌ አሳብ ስለተረዱ ይህንኑ መርህ በማይጻረር መልኩ ብድርን ሲያካሄዱ ቆይተዋል። የምሳሌዎችን አጠቃቀም ያውቁ ስለነበር፥ ይህ ክፍል ብድርን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው እንጂ ጭራሽ እንዲያስወግዱ ያላስተማራቸው መሆኑን ተገንዝበው ነበር።

ከላይ በሁለተኛነት ያቀረብነውም ምሳሌ (29፡12) በቀጥተኛ ትርጉሙ ተወስዶ ሊያደናግረን አይገባም። ይህ ምሳሌ የመንግሥት ባለሥልጣን የሆነ ሰው አለቃው (ገዥ፥ ፕሬዚዳንት ወይም ሌላ) ሰዎች የሚነግሩትን ውሸት የሚቀበል ከሆነ ከፉ ከመሆን ሌላ አማራጭ እንደሌለው የሚያስተምር አይደለም። ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት፥ ከእውነት ይልቅ ውሸትን ለመስማት የሚመርጥ መሪ የኋላ ኋላ በዙሪያው ለመስማት የሚፈልገውን የሚናገሩትን ሰዎች ሰብስቦ ይገኛል የሚል ነው። የዚህም ውጤት የተበላሸ መንግሥት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም፥ እያመመውም እንኳ እውነትን ለመስማት የሚመርጥ መሪ፥ መንግሥቱ ታማኝ እንዲሆን ያደርጋል። የምሳሌው ቃላት በቀጥተኛና በቴክኒካዊ መንገድ ሳይሆን በምሳሌያዊ መንገድ ይህንኑ መርህ ያሳያሉ።

ሦስተኛው ምሳሌ (15፡25) ምናልባትም ከሁሉም በላይ ቀጥተኛ እንዳልሆነ የምንረዳው ነው። ከራሳችን ገጠመኝም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት የትዕቢተኞች ቤት ጸንቶ ቆሞ መበለቶች በስግብግብ አበዳሪዎች ወይም አታላዮች ሲበደሉ እንመለከታለን (ማር. 12፡40፤ ኢዮብ 24፡2–3፥ ወዘተ...)። ይህ ምሳሌ የትዕቢተኞችን ቤት እንደሚያፈርስና የመበለቶች ጠባቂ እንደሆነ የሚናገር ካልሆነ፥ ምን ማለቱ ነው? ለማለት የፈለገው እግዚአብሔር ትዕቢተኛን እንደሚቃወምና ከችግረኞች (መበለቶች፥ እጓለማውታዎችና መጻተኞች የሚሉ ቃላት ለጥገኞች ሁሉ የሚያገለግሉ ናቸው። (ዘዳግ. 14፡29፤ 16፡11፤ 26፡12፥ 13፥ ወዘተ...) ጎን እንደሚቆም ነው። በተለይም ይህንን ምሳሌ ከምሳሌ 23፡10–11 እና ከሉቃስ 1፡52–53 ጋር ስናነጻጽር ፍችው በግልጽ ይታያል። ይህ መንፈስ ቅዱስ ከ«ቤት» እና ከ«መበለት» ባሻገር አጠቃላይ መርህ በማሳየት እግዚአብሔር የኋላ ኋላ ትዕቢተኞችን በመቅጣትና በጽድቅ የተንገላቱትን በመካስ የዚህን ዓለም የተሳሳቱ ነገሮች እንደሚያርም፥ የሚያመለክት ምሳሌ ነው (ማቴ. 5፡3–4 አንብብ)።

## ምሳሌዎች እንደ ስብስብ ሊነበቡ ይገባል

እያንዳንዱ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ያረፈበት ምሳሌ ከሌሎች ጋር በሚዛናዊነት ሊታይና ከተቀረው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሚጣጣም መልኩ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። ከላይ የተመለከትነው ሦስተኛው ምሳሌ (15፡25) እንደሚያሳየው፥ አንድን ምሳሌ ለብቻው በምናነብበት ጊዜ አሳቡ ግልጽ ላይሆንልን ይችላል። አንድን ምሳሌ ለብቻው ነጥለን ማንበቡ፥ ከሌሎች ጋር በምታነብበት ጊዜ ከሚሆነው የከፋ የባሕርይ ወይም የአመለካከት መዛባትን ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪም፥ ስለ ቁሳዊ ነገሮችና ስለዚህ ዓለም በትኩረት የሚያቀርቧቸው ተግባራዊ አሳቦች፥ ስለ ቁሳዊነትና ዓለማዊነት አደገኛነት የሚያስጠነቅቁትን ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊያዘነጋብህ አይገባም። ዓለማዊ ስኬትን በእግዚአብሔር ፊት የጽድቅ ምልክት አድርገህ በማሰብ እንደ ኢዮብ ጓደኞች መሳሳት የለብህም። ይህ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ሚዛናዊ ባልሆነ መንገድ ማንበብ ይሆናል። ከምሳሌዎች ውስጥ ለራስ ወዳድነት ወይም ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማይቀበሏቸው ባሕርያት ድጋፍ አትፈልግ። በተጨማሪም፥ ምሳሌዎች በተለያዩ መንገዶች በቡድን የተቀመጡ መሆናቸውንና እነዚህን በምታነብበት ጊዜ ከአንዱ ርእስ ጉዳይ ወደ ሌላው እየተላለፍህ መሆኑን አትዘንጋ። እነዚህ ሁሉ አሳቦች አንድ ሰው ከተሳሳተ አተረጓጎም እንዲርቅ የሚያስገነዝቡ ናቸው። አሁንም እነዚህን ሁለት ምሳሌዎች ተመልከት፡- (ምሳሌ 21፡22፤ 22፡14)።

ጠቢብ የኀያላንን ከተማ ቅጥር ጥሶ ይገባል፤

መታመኛ ምሽጋቸውንም ያፈርሳል።

የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጉድጓድ ነው፤

እግዚአብሔር የተቆጣውም ይገባበታል።

ጠቢብ ከሆንህ ከፍተኛ ጥበቃ ወደሚደረግባት ከተማ ጥሰህ በመግባት ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ታመጣለህ? እግዚአብሔርን ካስቀየምህ ወደ አመንዝራ ሴት ሰፊ አፍ የመግባት አደጋ ይጠብቅሃል?

ብዙ ሰዎች፥ «ምንም ይበሉ ምን እንደዚህ ማለታቸው ግን አይሆንም!» በማለት ለእነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ መልስ መስጠታቸው አይቀርም። ነገር ግን ሌሎች ብዙዎች ደግሞ ክርስቲያኖች ከብድር እንዲታቀቡ ለማስተማር ምሳሌ 22፡26ን፥ ወይም አንድ ሰው በየትኛውም ዕድሜ፥ የወላጆቹ ምክር ምንም ያህል የተሳሳተ ቢሆንም መቀበል እንዳለበት ለማሳየት ምሳሌ 6፡20ን በቀጥታ ሊወሰዱ እንደሚገባቸው ይከራከራሉ። ብዙ ሰዎች (የጋራ ግንዛቤ

ካለመጠቀማቸውም በላይ) ምሳሌዎችን እርስ በርሳቸውና ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር ባለማስተያየታቸው፥ ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ከፍተኛ የኢ-ፍትሐዊነት ተግባር ይፈጽማሉ።

ከላይ በቀረበው የመጀመሪያው ምሳሌ (21፡22)፥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት፥ ጥበብ ከወታደራዊ ኃይል ሊበልጥ እንደሚችል ነው። ይህ ግነታዊ አገላለጽ ነው። በስልቱ ይህ አባባል «ብዕር ከሰይፍ ይልቃል» የሚለውን ዘመናዊ ምሳሌ አይመስልም። ትእዛዝም አይደለም። ነገር ግን ተምሳሌታዊና ፈሊጣዊ የጥበብ ኃይል መግለጫ ነው። አንድ ሰው የዚህን ምሳሌ መልእክት የሚገነዘበው የጥበበን ጠቀሜታና ውጤታማነት የሚገልጹትን ሌሎች ምሳሌዎች (ምሳሌ፥ 1፡1-6፤ ምዕ. 2-3፥ 8፤22፡17-29፥ ወዘተ...) ካነበበ በኋላ ብቻ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው ሌላው ምሳሌ (22፡14) ከጠቅላላው ዓውደ ንባብ ጋር መነጻጸር አለበት። ብዙ ምሳሌዎች ስለ ንግግርና አሳብ ጥንቃቄ ያለበት አጽንኦት ሰጥተው ያስተምራሉ (ምሳሌ፥ 15፡1፤ 16፡10፥ 21፥ 23-24፥ 27-28፤ 18፡4፥ ወዘተ...)። በሌላ አገላለጽ፥ አንድ ሰው የሚናገረው ነገር ከሚሰማው በላይ ጥፋተኛ ያደርገዋል (ማቴ. 15፡11፥ 15-20)። የምትሰማውን ልትቆጣጠር ባትችልም፥ የምትናገረውን ልትቆጣጠር ትችላለህ። ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው በሌላ አገላለጽ ማቅረብ ይቻላል። «አንዲት አመንዝራ ሴት የምታደርጋቸውና የምትናገራቸው ነገሮች ከጥልቅ ጉድጓድ የመውደቅን ያህል አደገኞች ሊሆኑብህ ይችላሉ። የእግዚአብሔርን ቁጣ የምትፈራ ከሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱን ነገር አታድርግ።» የምሳሌዎቹን ዓውደ ንባብ መረዳቱ፥ በተሳሳተ መንገድ እንዳትተረጉመው ይረዳሃል።

### *ምሳሌዎች የተጻፉት እንዲታወሱ እንጂ፥ በንድፈ አሳባዊ ደረጃ ትክክል እንዲሆኑ አይደለም*

የትኛውም ምሳሌ ሙሉ የእውነት መግለጫ አይደለም። ማንኛውም ምሳሌ ሁልጊዜም በሁሉም ሁኔታ ውስጥ እንዲሠራ የሚጠየቅበትን ሚዛናዊ ያልሆነ አስተሳሰብ ለማሟላት ፍጹም ሆኖ አልተዘጋጀም። አንድ መርህ ይበልጥ አጠር ብሎ በምሳሌያዊ አገላለጽ ሲቀርብ፥ በአግባቡ ለመረዳት ይበልጥ የጋራ ግንዛቤንና ጥሩ ብያኔን ይጠይቃል። አሳቡ ግን ከሌላው በተሻለ ሁኔታ ውጤታማና ሊታወስ የሚችል ይሆናል። (ከላይ የቀረበውን ምሳሌ፥ «እሳት ለፈጀው ምን ይበጀው» ተመልከት።) መጽሐፈ ምሳሌ ሊያስተላልፍ የሚፈልገው መልእክት የአንድን ሃያሲ የሚያስደምም ፍልስፍና ሳይሆን፥ ለተግባራዊ አገልግሎት ሊውል የሚችል እውቀት ነው። ስለሆነም ምሳሌዎች የተዘጋጁት አንድም በአእምሮህ ውስጥ ምስል ለመከሰት (አእምሮ

ከረቂቅ አሳቦች በላይ ምስሎችን በተሻለ ሁኔታ ያስታውሳል) ወይም ለጆሮ የሚጥሙ ድምፆችን ለመጨመር (ማለትም ድግግሞሾች፥ የድምፅና የቀለም ተመሳሳይነት፥ እንዲሁም ስደራን የመሳሰሉት) ነው። የምስል መከሰትን ከምሳሌ 15፡19 ልትመለከት ትችላለህ።

የሐሰተኛ መንገድ በእሾህ የታጠረች ናት፤

የቅኖች መንገድ ግን የተጠራረገ አውራ ጎዳና ነው።

እዚህ ላይ ቋንቋው አንዳንድ ሰነፍ ሰዎች በሚወዱቸው መንገዶች ላይ የሚገኙትን ተክሎች ሳይሆን፥ ትጋት ከስንፍና እንደሚሻል የሚያመለክተውን መርህ ለማሳየት አገልግሏል።

በምሳሌ 31፡10–31 ላይ የተገለጸው የመልካም ሴት ባሕርይ የሆሄያዊ ስደራ ውጤት ነው። እያንዳንዱ ቁጥር ለዕብራውያን ጆሮ በሚጥሙና የመታወስ ብቃት ባላቸው ፊደላት የሚጀምር ሲሆን፥ አሳቡ ላልገባቸው ተችዎችና አንባቢያን የትኛዋም ግብረገባዊነት ያላት ሴት ልትከተል የማይገባትን ሞዴል ያቀርባል። ነገር ግን እንደ ምሳሌ 31፡22 ያለው ስልት፥ መልካም ሚስት ለቤተሰቧ የምታመጣውን ደስታ አጉልቶ ለማሳየት የቀረበበት ግነት መሆኑን ከተገነዘብን፥ ምሳሌያዊው ጥበብ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተግባሩን ያከናውናል። የምንባቡ ቃላትና ምስሎች ከአንባቢው ጋር ቆይተው አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተገቢውን ምሪት ይሰጣሉ። ምሳሌዎች እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ያቀደውም ይህንኑ ተግባር ነው።

*አንዳንድ ምሳሌዎች እንዲገቡን ወደ አሁኑ ዘመን*

*«ልንለውጣቸው» ይገባል*

ብዙ ምሳሌዎች መልእክቶቻቸውን የሚያስተላልፉት የብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን የለመዱቸውን ልማዶችና ተቋማት መነሻ አድርገው ነው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ አሁን የሉም። እነዚህን ምሳሌዎች ዛሬ ወዳሉት ልማዶችና ተቋማት «በመለወጥ» ከዘመናዊ አቻዎቻቸው አንጻር ካላሰብሃቸው፥ ትርጉማቸው ሊጨበጥልህ አይችልም። (ምዕ. 4 ተመልከት።) በተጨማሪ እነዚህን ሁለት ምሳሌዎች ተመልከት (ምሳሌ 22፡11፤ 25፡24)።

የልብ ንጽሕናን ለሚወድና ንግግሩም ሞገስ ላለው ሰው፣

ንጉሥ ወዳጁ ይሆናል።

ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር በአንድ ቤት ከመኖር፣

በጣራ ማዕዘን ላይ መኖር ይሻላል።

ብዙዎቻችን በነገሥታት በሚገዙ አገሮች ውስጥ አንኖርም። እንዲሁም፥ ደግሞ ከጣሪያ ላይ መኖር የሚቻል ብቻ ሳይሆን የተለመደ ባሕል የሆነባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ቤቶች የሉንም (ኢያሱ 2፡6)። እንግዲህ፥ እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎችን ማንበብ ጊዜ ማባከን ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱሱ ባሕል ጉዳዮች በራሳችን ባሕል ከተገለጹ፥ እነዚህን ምሳሌዎች ማንበቡ ከቶውንም ጊዜ ማባከን ሊሆን አይችልም። የመጀመሪያው ምሳሌ ዋና መልእክት (22፡11) ከንጉሡ ጋር መወዳጀት የሚለውን በአሁኑ ዘመን አመራር ላይ ያሉት ሰዎች ስለ እኛ አዎንታዊ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ማድረግ በሚል አሳብ ከተቀየረ፥ ለመገንዘብ የሚከብድ አይሆንም። ምሳሌው ሁልጊዜም ይህንኑ አሳብ ያስተላልፋል። ንጉሥ መሪዎችን ሁሉ ይወክላል። የምሳሌው ውስን ምሳሌያዊ ቋንቋ ከራሱ አልፎ መሪዎችና ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች በታማኝነትና ንግግርን በጥንቃቄ በማቅረብ የሚደሰቱ መሆናቸውን ለማሳየት የሚያገለግል ነው።

ሁለተኛው ምሳሌ (25፡24) ከዚያ በኋላ ወደ እኛው አስፈላጊውን ሽግግር ካካሄድን ለመረዳት ብዙም የሚያስቸግር አይደለም። እንዲያውም፥ እንደሚከተለው በሌላ አገላለጽ ልናቀርበው እንችላለን፤ «ባላገባኋት ብለህ ከምትቆጭ ሴት ጋር በሰፊ ቤት ውስጥ ከመኖር በጋራዥ ውስጥ መኖር ይሻላል።» የአብዛኞቹ ምሳሌዎች ምክር የተሰጠው ሕይወትን ገና ለሚጀምሩ ወጣቶች እንደሚመስል አስታውስ። ምሳሌው የተሰጠው ጨቅጫቃ ሚስት ያለችው ምን ማድረግ እንዳለበት ለመምከር አይደለም። ይልቁንም ሰዎች የትዳር ጓደኞቻቸውን በጥንቃቄ እንዲመርጡ ለመምከር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ምርጫ ባሕላዊ ምርጫ መሆኑን በመገንዘብ መጽሐፈ ምሳሌ ጠቃሚ መንፈሳዊ ምክሮችን ይሰጣል። (ማቴ. 19፡3-11፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡1-14፥ 25-40 አንብብ።) በአካላዊ መስህብነት ላይ የተመሠረተ የጥድፍያ ጋብቻ የኀዘን ሸለቆ ሊሆን እንደሚችል መገንዘቡ ጠቃሚ ነው።

ከዚህ በታች ምሳሌዎችን በአግባቡ እንድትጠቀምና በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ሊተላለፍ የተፈለገውን ፍች እንድትከተል የሚረዱህን አንዳንድ መመሪያዎችን በማጠቃለያ መልክ አቅርበንልሃል።

1. ብዙውን ጊዜ ምሳሌዎች ከራሳቸው ወዲያ የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አገላለጾች ናቸው።

2. ምስሌዎች በንድፈ አሳባዊ መልኩ ሥነ መለኮታውያን ሳይሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ተግባራውያን ናቸው።

3. ምሳሌዎች የተጻፉት ለረዥም ጊዜ እንዲታወሱ እንጂ የተፈለገውን መልእክት በሙሉ እንዲያካትቱ ተደርገው አይደለም።

4. ምሳሌዎች የራስ ወዳድነትን ባሕርይ የሚደግፉ ሳይሆኑ፥ እንዲያውም የእዚያ ተገላቢጦሽ የሆነውን መልእክት የሚያስተላልፉ ናቸው።

5. የጥንቱን ባሕል በስፋት የሚያንጸባርቁ በመሆናቸው፥ ትርጉማቸው እንዳይሰወር ወደ ዘመናችን ልንለውጣቸው ይገባል።

6. ምሳሌዎች ለመልካም ባሕርይ ቅኔያዊ መመሪያዎች እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡ ዋስትናዎች አይደሉም።

7. ምሳሌዎች መልእክታቸውን ለማስተላለፍ ውስን፥ ግነታዊ ወይም የትኛውንም የሥነ ጽሑፋዊ ቴክኒኮች አካል የሆነውን የቋንቋ ስልት ሊጠቀሙ ይችላሉ።

8. ምሳሌዎች የተወሰኑ የሕይወት ገጽታዎችን በጥበብ መንገድ ስለ መምራት ጥሩ ምክሮችን ቢሰጡም፥ ሁሉንም የሕይወት ገጽታዎች አያካትቱም።

9. ምሳሌዎች፥ በተሳሳተ መንገድ ከተጠቀምንባቸው የቁሳዊነትን ሕይወት ተገቢነት የሚያስተምሩ ሊመስሉ ይችላሉ። በአግባቡ ከተጠቀምንባችው ግን ለዕለታዊ አኗኗራችን ተግባራዊ ምክሮችን ሊሰጡን ይችላሉ።

## ጥበብ በመኃልየ መኃልይ ውስጥ

መኃልየ መኃልይ ረዥም የፍቅር መዝሙር ነው። መዝሙሩም በጥንታዊ የምሥራቅ አገሮች የስሜት መግለጫ ስልት የተጻፈ ረዥም የፍቅር ግጥም ነው። ይህንን ስሜታዊ ጥበብ ልንለው እንችላለን። እንደ ሌሎች አገር ሰዎች ሁሉ በጥንታዊት እስራኤል የነበሩ ሰዎችም የፍቅር ዜማዎችን ያዘወትሩ ነበር (ሕዝ. 33፡32 አንብብ)። ነገር ግን የፍቅር ዝማሬ በጥበብ ምድብ ውስጥ የሚገባው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ስምንቱን የፍቅር ምዕራፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያስቀመጠው ለምንድን ነው? ለእዚህ መልሱ ቀላል ነው። መዝሙሩ ያተኮረባቸው ማንን ላፍቅር? እና እንዴት ላፍቅር? የሚሉ ጥያቄዎች በሕይወት ውስጥ እጅግ መሠረታዊ ጉዳዮች በመሆናቸው ነው። ለእነዚህ ሁለት ወሳኝ ውሳኔዎች መንፈሳዊ ምርጫዎችን ማድረግ ደግሞ ለማንኛውም አማኝ እጅግ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የፈጠረው ብዙ የጭንቅላት ሕዋሳቶቹ (ሴሎቹ) በፍቅርና ወሲብ ላይ እንዲያተኩሩ አድርጎ ነው። ይህ የሰብአዊነታችን እውነታ ሲሆን፥ እግዚአብሔርም «መልካም ነው» ብሎ ያወጀው ሰብአዊ ፍጥረታችን ነው (ዘፍጥ. 1፥31)። ነገር ግን የትኛውም መልካም ነገር በመንፈሳዊ መንገድ ካልተመረጠ መበላሸቱ አይቀርም። የትኛውም የሰው ችሎታ ለመልካምም ሆነ ለመጥፎ ነገር ሊውል የሚችል ሲሆን፥ የትኛውም የሰው ልጅ ፍላጎት ከትክክለኛው ይልቅ የተሳሳተውን አቅጣጫ ሊከተል ይችላል። ፍቅርና ወሲብም እንዲሁ ነው። እነዚህም በሰው ልጆች ውድቀት ምክንያት የተበላሹ በመሆናቸው፥ እግዚአብሔር እንዳቀደው ሁልጊዜም በአንድ ለአንድ ጋብቻ ውስጥ የደስታና የበረከት ምንጭ ከመሆን ይልቅ፥ ብዙውን ጊዜ የራስ ወዳድነት መግለጫዎች ሆነዋል። በዚህም ለሁሉም ዓይነት ምኞቶችና ብዝበዛዎች ክፍት ሆነዋል። ወሲብን አስመልክቶ ሰዎች ብዙ ምርጫዎች አሏቸው። አንድ ሰው ውጤቶቹን ሳያመዛዝን ያገኘውን የወሲብን ጎዳና ተከትሎ ብቻ መሄድ ይችላልን? ደግሞስ ሰዎች እግዚአብሔርን የማያስከብር ወሲብ ይፈጽማሉን? ያለጥርጥር ይፈጽማሉ። እንዲሁም ግብረ ሥጋን ከአግባብ በሳተ መንገድ ማድረግ ጉዳት አለበት? አዎ ጉዳት አለበት። ወሲብ የጭካኔና የራስ ፍላጎት መገለጫ ሊሆን ይችላል? በሚገባ በአካላዊ ቴክኒክ ላይ የሚደረገው አጽንኦት የወሲብን የፍቅር ስሜት በተሳሳተ መንገድ ሊተካው ይችላል? አዎን ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በፍቅር ውስጥ ሊኖሩ አይገባም። እግዚአብሔር ትክክለኛ ምርጫዎች ከተካሄዱ ፍቅርና ወሲብ እግዚአብሔር መጀመሪያ የወጠነውን ዕቅድ በመፈጸም ለእርሱ ክብር ሊውል ይችላል። የመኃልየ መኃልይ መልእክትም ይኸው ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ መዝሙር በሁለት ሥነ አፈታታዊ ስሕተቶች ላይ የተመሠረተ ግራ የሚያጋባ የአተረጓጎም ታሪክ አለው። እነዚህ ሁለት ስሕተቶች ሁሉን አቀፍ ሽግግር (totality transfer) እና ስውር መንፈሳዊ ፍች የሚፈለግበት አለጎሪ ናቸው። ሁሉን አቀፍ ሽግግር ሲባል የአንድ ቃል ወይም ጽንሰ አሳብ አማራጭ ፍችዎችና ገጽታዎች ሁሉ ቃሉ ወይም ጽንሰ አሳቡ በሚያገለግልበት ጊዜ አብረው ሊገኙ ይገባል የሚል ዝንባሌ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን «እግዚአብሔር ዓለምን ስለወደደ» የሚለው ሐረግ የወሲባዊ ፍቅርንም ገጽታ እንደሚያመለክት ማሰብ ይሆናል። ይህም «ፍቅር» የሚለው ቃል በሚያገለግልበት ስፍራ ሁሉ የወሲብን አሳብ እንደሚያመለክት በመታሰቡ ነው። ይህ በተለይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምንም የወሲብ አሳብ ለማይገለጽባቸው ዕቃዎችም ስለሚያገለግል የሁሉን አቀፍ ሽግግርን አስተሳሰብ ጉድለት ያመለክታል። አንድ

የእንግሊዝኛ ተናጋሪ «የኦቾሎኒ ቅቤ አፈቅራለሁ» ("I just love peanut butter") ሊል ይችላል። እዚህ ላይ «ፍቅር» የሚለው ቃል ምንም ዓይነት ወሲባዊ መልእክት እንደሌለው ግልጽ ነው።

በመኃልየ መኃልይ ሁሉን አቀፍ ሽግግር የተካሄደው ከሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የፍቅር መዝሙሮች ነው። ሰዎች መጀመሪያ ከመኃልየ መኃልይ ጋር የሚመሳሰል ነገር በሚፈልጉበት ጊዜ ያገኟቸው አንዳንድ ምንባቦች የተገኙት ከነቢያት ትንቢታዊ አለጎሪዎች ነበር። እነዚህ አለጎሪዎች በፍቅር መዝሙር መልክ የተዘጋጁ ሲሆኑ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡ እስራኤላውያንን እንዴት እንዳፈቀራቸውና እነርሱ ግን ፍቅርን ለመቀበል እንዳልፈለጉ ያስረዳሉ። በሌላ አገላለጽ፥ በመኃልየ መኃልይ ውስጥ የምንመለከታቸው ዓይነት ቃላትና ምሳሌዎች ስለ እግዚአብሔርና እስራኤል ግንኙነቶች በሚናገሩ የነቢያቱ አለጎሪያዊ ትንቢቶች ውስጥ ይገኙ ነበር። ለዚህም ምሳሌዎች የሚሆኑን ምንባቦች በኢሳይያስ 5፡1–7 እና ሆሴዕ 2፡2–15 በግጥም መልክ ሲቀርቡ፥ በሕዝቅኤል 16 እና 23 በዝርው ጽሑፍ መልክ ረዘም ብለው ተገልጸዋል። ከእነዚህ ትንቢታዊ የፍቅር መዝሙሮች በመነሣት የቀድሞዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ወደ አንድ ድምዳሜ አመሩ። በመሆኑም፥ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የፍቅር መዝሙራት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሕዝቡ የሚናገሩ አለጎሪዎች ከሆኑ፥ እንደ መኃልየ መኃልይ ዓይነቱ የፍቅር መዝሙርም ከዚህ የተለየ ሚና ሊኖረው አይችልም ብለው አሰቡ። የሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስውር ምሥጢራት የመፈለጉ አለጎሪያዊ አተረጓጎም በተስፋፋበት ዘመን (በዚህ መጽሐፍ ገጽ 139–140 ተመልከት)፥ ጥሩ አሳብ ቢኖራቸውም የተሳሳተ ግንዛቤ ያልተለያቸው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መኃልየ መኃልይ እግዚአብሔር ለእስራኤል ወይም ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር የሚገልጽ አለጎሪ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም ከሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ። ይህም አተረጓጎም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሲሠራበት ቆይቷል።

ነገር ግን ላይ ላዩን ሲታይ እንኳ መኃልየ መኃልይ የሚያስተላልፈው መልእክት ይኼ አይደለም። አለጎሪያዊ የፍቅር መዝሙሮች እንደሚገኙባቸው ትንቢታዊ መጻሕፍት ካለመሆኑም በላይ፥ እንደ እነርሱ በግልጽ አለጎሪካል አይደለም። ትንቢታዊ አለጎሪዎች እንደሚያደርጉት ወደ እስራኤል ታሪክ የሚያመለክቱትን የተለያዩ ፍንጮች አይሰጥም። በተጨማሪም፥ እንደ እነርሱው በብሔራዊ ተምሳሌታዊነት አልተጨናነቀም። ይልቁንም፥ በአንዲት ሴትና በአንድ ወንድ የፍቅር ግንኙነት ላይ በማተኮር በመካከላቸው የሚታየውን የፍቅር ስበት ይተርካል። ይህንንም የሚያደርገው ሰፋ ባለ

መልኩ በመሆኑ፥ ከትንቢታዊ መዝሙሮች የተለየ ነው። ለምሳሌ፥ በነቢያት ውስጥ የሚከተለውን የሚመስል ምንባብ የለም።

ወዳጄ ሆይ፥ እነሆ፥ ውብ ነሽ
እነሆ፥ አንቺ ውብ ነሽ
በዓይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ ዓይኖችሽ እንደ ርግቦች ናቸው።
ጠጉርሽ በገለዓድ ተራራ እንደሚወርድ እንደ ፍየል መንጋ ነው።
ጥርሶችሽ ታጥበው እንደ ተሸለቱ ሁሉም መንታ እንደ ወለዱ
ከእነርሱም መካን እንደሌለባቸው መንጎች ናቸው።
ከንፈሮችሽ እንደ ቀይ ሐር ፈትል ናቸው።
አፍሽም ያማረ ነው።
በዓይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ ጉንጭና ጉንጭሽ እንደ ተከፈለ ሮማን ናቸው።
አንገትሽ ለሰልፍ ዕቃ መስቀያ እንደተሠራው እንደ ዳዊት ግንብ ነው።
ሺህ ጋሻ የኃያላንም መሣሪያ ሁሉ ተንጠልጥሎበታል

(መኃ. 4፡1–4)።

ይህ አንድ ሰው ፍቅረኛውን የሚያደስበት አገላለጽ ነው። በዚህ አገላለጹም አካላዊ ገጽታዋን በሕይወት ውስጥ ምርጥ ናቸው ከተባሉ ነገሮች ጋር ያነጻጽራል። የሚናገረው ቁርጥ እርሱን ስለሚመስሉት ነገሮች ሳይሆን፥ እንደ እርሷው ዓይነግቡ ስለሆኑት ነገሮች ነው።

በነቢያት የፍቅር መዝሙሮች ውስጥ የመኃልየ መኃልይ ዓይነት አገላለጽ እንደሌለ ለማሳየት የሚከተለውን እንደ ተጨማሪ መረጃ እንጠቅሳለን፡—

እኔ ተኝቻለሁ፥ ልቤ ግን ነቅቶአል!
የውዴ ቃል ነው፥ እርሱም ደጁን ይመታል!
እኅቴ፥ ወዳጄ፥ ርግቤ፥ መደምደሚያዬ ሆይ፥
በራሴ ጠል፥ በቈንዳላዬም የሌሊት ነጠብጣብ ሞልቶበታልና ክፈችልኝ።
ቀሚሴን አወለቅሁ! እንዴት እለብሰዋለሁ?
እግሬን ታጠብሁ! እንዴት አሳድፈዋለሁ?
ውዴ እጁን በቀዳዳ ሰደደ፥
አንጀቴም ስለ እርሱ ታወከ።

ለውዴ እከፍትለት ዘንድ ተነሣሁ፤
እጆቼ በደጁ መወርወሪያ ላይ ከርቤን አፈሰሱ፥
ጣቶቼ ፈሳሹን ከርቤ አንጠባጠቡ።
ለውዴ ከፈትሁለት፥
ውዴ ግን ፈቀቅ ብሎ አልፎ ነበር (መኃ. 5፡2–6)።

ይህ አንዲት ሴት እንዴት እንዳንቀላፋችና ፍቅረኛዋ በጠራት ጊዜ በፍጥነት ተነሥታ ልትከፍትለት እንዳልቻለች የሚገልጽ የሕልም ታሪክ ነው። «እያለምሁ ነበር» ለማለት የተጠቀመችበት ቅኔያዊ አገላለጽ፥ «እኔ ተኝቻለሁ፥ ልቤ ግን ነቅቶአል» የሚለው ነው። እኛም እንደዚሁ ቶሎ ለመነሣት ወይም በጣም የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት የማንችልባቸው ሕልሞች አሉን። እዚህ ጋ ሕልሙ ሴቲቱ ወደ ፍቅረኛዋ እንዴት እንደምትሳብና ከእርሱ ጋር ለመሆን የምትችልበትን ዕድል ማጣቷ እንዴት አሳዛኝ እንደሆነ ለማመልከት ያገለግላል። (በተጨማሪም 3፡1–5ን ተመልከት)።

በመኃልየ መኃልይ ውስጥ ከአካላዊ ንጽጽሮችና የሕልም ትእይንቶች በተጨማሪ ሌሎችም የፍቅር መግለጫዎች አሉ። በተጨማሪም፥ የፍቅር ስሜት (ምሳሌ፥ 1፡2–4)፥ የፍቅር ታዛቢዎች ምክርና ጥያቄ (ምሳሌ፥ 1፡8፤ 5፡9)፥ ከወንዱ ለሴቷና ከሴቷ ለወንዱ የፍቅር ግብዣዎች (ለምሳሌ፥ 7፡11–13፤ 8፡13)፥ ወንዱ ስለ ሴቲቱ፥ ሴቲቱ ደግሞ ስለ ወንዱ የሚያቀርቧቸው ውዳሴዎች (ምሳሌ፥ 2፡8–9)፥ ወደ ሌሎች በፍቅር የመሳብን ፈተና የማስወገድ አስፈላጊነት (ምሳሌ፥ 6፡8–9)፥ እና የፍቅረኛ ማራኪነት እንደ ሰሎሞን ካለው ንጉሥ ክብር እንኳ እንደሚበልጥ የተገለጸባቸው ክፍሎች አሉ። እነርሱም፡– (ምሳሌ፥ ከ2፡16–3፡5 የቀጠለውን 3፡6–11 ከ8፡11–12 ጋር አነጻጽር)። እነዚህ ሁሉ እንደ ሙዚቃዊ ግጥም የቀረቡ ቢሆኑም፥ ስለ ፍቅርና ወሲብ ከሚኖሩ የሕይወት ምርጫዎች ጋር በአመክኒዮአዊ መንገድ የተዛመዱ ናቸው።

እዚህ ላይ መኃልየ መኃልይን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚፈልገው ለመረዳት ያስችሉሃል ብለን የምናስባቸውን አሳቦች እንደሚከተለው አቅርበናል።

በመጀመሪያ፥ የመኃልየ መኃልይን አጠቃላይ የግብረገብነት ዓውድ ለመረዳት ሞክር። ከብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር መገለጥ አንጻር፥ ለወሲባዊ ግንኙነት ትክክለኛው ዓውድ አንድ ለአንድ የሚካሄድ የሁለቱ ፆታዎች ጋብቻ ስለነበር፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እስራኤላውያን መኃልየ መኃልይን ከዚህ አንጻር ይገነዘቡት ነበር። የመኃልይ አመለካከት ራሱ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ ታማኝነት ማጎደልን የሚቃወም ነው። ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት

መካከል የሚኖረውን ፍቅር ወደ ምልዓት የሚያመጣና የሚቀጥል ነገር ነው። መኃልየ መኃልይም የሚያመለክተው ይህንኑ ነው።

ሁለተኛ፥ የመኃልየ መኃልይን ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ አስተውል። የዚህ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የቅርብ ተመሳሳዮች በብሉይ ኪዳንና በጥንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የነበሩ የፍቅር ግጥሞች ነበሩ። የእነዚህም ዓውድ ማንኛውንም ዓይነት ፍቅር መዘከር ሳይሆን፥ ወደ ጋብቻ መሳብ ነበር። የፍቅር መዝሙሮች ምናልባትም በሠርግ በዓላት ላይ እየተዘመሩ ለበዓሉ ተካፋዮች ከፍተኛ ትርጉም ሳይሰጡ አይቀሩም። እነዚህ መዝሙሮች በፍቅር ስለ መሳሳብ፥ ታማኝነት፥ የማታለልን ፈተና ስለ መቋቋም፥ ስለ ፍቅር ታላቅነት፥ ስለሚያስከትላቸው የደስታና የእርካታ ፍሬዎች፥ ብሎም ስለ ታማኝነት ጉድለት አደጋዎች የሚናገሩ ናቸው። መዝሙሮቹ ጠንካራ ግብረገባዊ ድምፀቶች ያሏቸው ሲሆኑ፥ የፍቅር ግንኙነት በትክክለኛ ዓውድ ሊካሄድ እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ሦስተኛ፥ መኃልየ መኃልይ መንፈሳዊ ምርጫዎችን እንደሚገልጽ ሳይሆን፥ እንደሚያደፋፍር አድርገህ አንብብ። ይህ መጽሐፈ ምሳሌን ስለ መተርጎም ከገለጽነው አሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው። ልናደርጋቸው ስለሚገቡን ነገሮች አሳብ የሚሰጡና ጠቅለል ባለ መልክ የቀረቡ እንጂ የአንድ ሐቅ ትክክለኛ መግለጫዎች አይደሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመኃልየ መኃልይ ጋር በጣም ከሚመሳሰሉት ክፍሎች አንዱ ምሳሌ 1–9 ነው። በዚህ ክፍል ስለ ጥበብ ማራኪነትና ስለ ሞኝነት አስቀያሚነት የሚገልጹ አሳቦች ስሜትን በሚኮረኩር መንገድ ተገልጸዋል። ይህም ትክክለኛ አመለካከታችን እንዴት ሊሆን እንደሚገባ የሚያሳይ ነው።

አራተኛ፥ መኃለየ መኃልይ ከእኛ ዘመናዊ ባሕል በሚለዩ እሴቶች ላይ እንደሚያተኩር ተገንዘብ። ዛሬ ባለሙያዎች (ኤክስፐርቶች) የሚናገሩት ስለ ወሲብ ቴክኒኮች እንጂ ወንድንና ሴትን ወደ ዘለቄታዊ ትዳር ስለሚመራው ትክክለኛ ፍቅር አይደለም። እንዲህ ዓይነቶቹ ባለሙያዎች የራስን ምኞት እንዴት ማሟላት እንደሚቻል ሊያስተምሩ ይችላሉ። ይህም የመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ የሚቃወመው ነው። ዘመናዊው ባሕል ሰዎች ወሲባዊ ፍላጎታቸው ምንም ዓይነት ቢሆን ራሳቸውን እንዲያረኩ ያበረታታል። መኃልየ መኃልይ ግን አንድ ሰው እንዴት ለሌላው ሰው ማራኪነት በታማኝነት ምላሽ ሊሰጥ እንደሚገባና የሌላውን ፍላጎት እንደሚያሟላ ያስተምራል። በአብዛኛው ዘመናዊ ዓለም፥ ፍቅር ከጋብቻ እንደሚቀድም ይታሰባል። በመኃልይ ግን ፍቅር በጋብቻ ሕይወት ሁሉ ሊቀጥልና እንዲያውም የጋብቻ መለያ ሊሆን እንደሚገባ ተገልጾአል። የሁላችንም ትዳር እንዲህ ሊሆን ይገባል።

# የዮሐንስ ራእይ፡ የፍርድና የተስፋ ምስሎች

አንድ ሰው ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች አልፎ ወደ ዮሐንስ ራእይ በሚደርስበት ጊዜ፥ ወደ ውጭ አገር እንደ ሄደ ሊሰማው ይችላል። ግልጽ የእውነትና የትእዛዝ አሳቦችን ከሚያስተላልፉ ትረካዎችና መልእክቶች፥ መላእክት፥ መለከቶች፥ የምድር መንቀጥቀጥ፥ አራዊት፥ ዘንዶዎችና ጥልቁ ጉድጓድ ወደሞሉበት መጽሐፍ ይመጣል።

ሥነ አፈታታዊ ችግሮች የመጽሐፉ ባሕርይ አካላት ናቸው። መጽሐፉ በቀኖና ውስጥ ስለሚገኝ፥ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ያረፈበት የእግዚአብሔር ቃል ነው። ነገር ግን ያንን ቃል ለመስማት በምንጥርበት ጊዜ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎቻችን ከመጽሐፉ ምን እንደምናገኝ አናውቅም። ደራሲው አንዳንድ ጊዜ፥ «እኔ ወንድማችሁ ዮሐንስ፣ ከእናንተ ጋር አብሬ በኢየሱስ መከራውንና መንግሥቱንም ተካፋይ የሆንሁ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክርነት ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ» (1፡9) ሲል በቀጥታ ይናገራል። ሊታወቁ በሚችሉ የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ሁኔታዎች ውስጥ በታወቁ ከተሞች ለነበሩት ሰባት የታወቁ አብያተ ክርስቲያናት ጽፎአል።

በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ልዩ ልዩ ጥልቅ ተምሳሌቶችን ተጠቅሟል። ከእነዚህም ተምሳሌቶች አንዳንዶቹ ሊታወቁ የሚችሉ ሲሆኑ (ፍርድ በምድር መንቀጥቀጥ መልክ፤ 6፡12–17)፥ ሌሎቹ ግን ለመረዳት የሚያዳግቱ ናቸው (ሁለቱ ምስክሮች፤ 11፡1–10)። አብዛኞቹ የግንዛቤ ችግሮች የሚመጡት ከተምሳሌቶች፥ ብሎም መጽሐፉ ስለ ወደፊት ክስተቶች እየተናገረ ሊታወቅ በሚችል የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ዓውድ ውስጥ ከመገኘቱ ነው።

በዚህ ምዕራፍ የዮሐንስ ራእይን ችግሮች ሁሉ እንፈታለን አንልም። እንዲሁም ደግሞ ሁሉም አንባቢዎች እኛ ከምንለው ጋር ይስማማሉ ብለን አናስብም። ማንም ሰው ተገቢውን ራስን ዝቅ የማድረግ አመለካከት ከመላበሱ በፊት ራእይን ለመረዳት መሞከር እንደሌለበት ገና ከመጀመሪያው ግልጽ ሊሆን ያሻል! እስካሁን (በተለይ በውጭ አገር) «ራእይን በቀላሉ ለማስረዳት» የሚሞክሩ ብዙ መጻሕፍት ታትመዋል። ይህም ሆኖ፥ የራእይን መልእክት መረዳቱ ቀላል አልሆነም። በመልእክቶች ውስጥ እንደሚገኙ አስቸጋሪ

ምንባቦች ሁሉ (ምዕራፍ 3ን ተመልከት)፥ በዚህ መጽሐፍም አንድ ሰው ሁሉንም ነገር አውቃለሁ የሚል ግትር አቋም ሊይዝ አይችልም። ለዚህም ምክንያቱ በውስጣቸው የሚገኙትን ክፍሎች ከግንዛቤ ውስጥ ሳናስገባ ቢያንስ አምስት የአተረጓጎም ፍልስፍናዎች መኖራቸው ነው።

ነገር ግን ዮሐንስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት አስመልክቶ የጠራ ግንዛቤ እንዳለን እናስባለን። ስለሆነም ለእኛ ጠቃሚዎች የመሰሉንን አንዳንድ ሥነ አፈታታዊ አሳቦች እናቀርብልሃልን። ነገር ግን ቀድሞ የሚመጣው ሐቲት ሲሆን፥ በተለይ ለዚህ መጽሐፍ ሐቲት ወሳኝ ነው። ይህ ብዙ ተወዳጅ መጻሕፍትና ትራክቶች የተጻፉለት መጽሐፍ ነውና። ሁልጊዜም ማለት ይቻላል እነዚህ ተወዳጅ መጻሕፍት ስለ ራእይ ሐቲታዊ ዘዴ ሲጠቀሙ አንመለከትም። በጥድፍያ የሚያቀርቧቸው ሥነ አፈታታዊ አሳቦችም ቢሆኑ ዮሐንስ ሊረዳቸውም ሆነ ሊያስተላልፍ የፈለጋቸው አይመስሉም።

## የራእይ ባሕርይ

እንደ ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሥነ ጽሑፍ ቅርጾች ሁሉ፥ ለዮሐንስ ራእይም የመጀመሪያው ቁልፍ የሥነ ጽሑፉን ዓይነት መመርመር ነው። ነገር ግን ራእይ ከሦስት የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች የተገነባ በመሆኑ የተለየ ችግር ያጋጥመናል። እነዚህም ሦስት የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች ሥዕላዊ (ኤፖካሊፕስ)፥ ትንቢታዊና ደብዳቤያዊ ናቸው። ከዚህም በላይ በራእይ ውስጥ በመሠረታዊነት ያገለገለው ኤፖካሊፕስ በዘመናችን የሌለ የሥነ ጽሑፍ ዓይነት ነው። የቀደሙት የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን አስመልክቶ የእኛዎቹ ምሳሌዎቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተወሰዱት ቢለዩም፥ ስለ መልእክት፥ ትረካ፥ መዝሙር ወይም ስለ ምሳሌ ምንነት መሠረታዊ ግንዛቤዎች አሉን። ነገር ግን ኤፖካሊፕስን የሚመስል ነገር የለንም። ስለሆነም፥ እያጠናን ስላለነው የሥነ ጽሑፍ ዓይነት ግልጽ ግንዛቤ መጨበጡ ጠቃሚ ነው።

### *ራእይ እንደ ኤፖካሊፕስ*

ራእይ በቀዳሚነት ኤፖካሊፕስ (ራእያዊ ጽሑፍ) ነው። ነገር ግን አይሁዶችና ክርስቲያኖች ከ200 ዓ.ዓ. እስከ 200 ዓ.ም. ያውቋቸው ከነበሯቸው በደርዘን ከሚቆጠሩ የራእያዊ ጽሑፍ ዓይነቶች፥ በራእይ ውስጥ የምናገኘው አንደኛውን ብቻ ነው። እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ያልታቀፉ ሌሎች የራእያዊ ጽሑፍ ዓይነቶች የተለያዩ ዓይነቶች ቢሆኑም፥ ራእይን ጨምሮ ሁሉም አንዳንድ የጋራ ባሕርያት አሏቸው። እነዚህ የጋራ ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው፡—

1. የራእያዊ ጽሑፍ ሥነ ጽሑፍ መሠረቱ የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ ጽሑፍ ነው። ይህም በተለይ በሕዝቅኤል፥ በዳንኤል፥ በዘካርያስና በአንዳንድ የኢሳይያስ ክፍሎች የሚገኝ ነው። በአንዳንድ ራእያዊ ጽሑፎች ውስጥ እንደሚታየው፥ ዋና ትኩረቱ መጭው ፍርድና ደኅንነት ነው። ነገር ግን ራእያዊ ጽሑፍ የተወለደው በስደት ወይም በከፍተኛ የጭቆና ወቅት ነበር። ስለሆነም አጽንኦት የሚሰጠው እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት አይደለም። ነገር ግን የራእያዊ ጽሑፍ ጸሐፊዎች የሚመለከቱት እግዚአብሔር ታሪክን ወደ ፍጻሜ ወደሚያመጣበት፥ ትክክለኛነትና በክፉዎች ላይ ፍርድ ወደሚሰጥበት የወደፊት ዘመን ነው።

2. ከአብዛኞቹ የትንቢት መጻሕፍት በተቃራኒ፥ ራእያዊ ጽሑፎች ከመጀመሪያው ጀምሮ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ናቸው። ነቢያት በመሠረታዊነት ለእግዚአብሔር በቃል አቀባይነት ያገለግሉ የነበሩ ሲሆን፥ በኋላ ተሰብስበው በመጻሕፍት መልክ የታተሙት ሥራዎቻቸው መጀመሪያውኑ በቃል የተናገሯቸው ነበሩ። ኤፖክሊፕስ ግን የሥነ ጽሑፍ ዓይነት ነው። ነቢያት የተነገራቸውን ወይም ያዩትን ለሕዝቡ እንዲናገሩ የታዘዙ ሲሆን፥ ዮሐንስ ግን ያየውን እንዲጽፍ ተነግሮታል (1፡19)።

3. ብዙውን ጊዜ ራእያዊ ጽሑፍ ስውር ምሥጢርና ተምሳሌት የያዘ ሲሆን፥ በራእዮችና ሕልሞች መልክ ይቀርባል። ስለሆነም አብዛኞቹ ራእያዊ ጽሑፎች ለመጽሐፉ ጥንታዊነት የሚሰጡ ሥነ ጽሑፋዊ መሣሪያዎችን ያካተቱ ናቸው። ከእነዚህም መሣሪያዎች በጣም አስፈላጊው እንደ ሄኖክ፥ ባሮክ፥ የመሳሰሉት ጥንታዊ ጸሐፊዎች «ለኋለኛው ዘመን እንዲታተም» የተናገሩ መሆናቸውን መግለጽ ነበር። «የኋለኛው ዘመን»ም አሁን መጽሐፉ የሚጻፍበት ዘመን ነው።

4. የራእያዊ ጽሑፍ ምስሎች ብዙውን ጊዜ ሕልማዊ እንጂ እውናዊ አይደሉም። ኤፖክሊፕቲካዊ ያልሆኑ ዘዴዎችን የተጠቀሙት ነቢያትና ክርስቶስም ተምሳሌታዊ ባልሆኑት ቋንቋዎች መልእክቶቻቸውን ማስተላለፋቸው ይታወቃል። ነገር ግን ክርስቶስና ሌሎችም የተጠቀሙባቸው ተምሳሌቶች ጨው (ማቴ. 5፡13)፥ አሞራዎችና ጥንብ (ሉቃስ 17፡37)፥ ሰነፍ ርግቦች (ሆሴዕ 7፡11)፥ በአንድ በኩል ያረረ ቂጣ (ሆሴዕ 7፡8) የመሳሰሉ እውነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። የራእያዊ ጽሑፍ ምሳሌዎች ግን ወደ ሕልም ዓለም የሚሄዱ ናቸው። ከእነዚህም መካከል፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት አውሬ (ራእይ 13፡1)፥ ፀሐይን የተጎናፀፈች ሴት (ራእይ12፡1)፥ የጊንጥ ጅራትና የሰው ፊት ያላቸው አንበጦች (9፡10) ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሕልምነቱ የሚታየው ምድራዊ ካልሆነው ቅይጥነታቸው እንጂ ከነገሮቹ

አይደለም። በመሠረቱ (አውሬዎች፥ ራሶችና ቀንዶች የምናውቃቸው ነገሮች ናቸው።)

5. ራእያዊ ጽሑፎች ጥበባዊ ሥራዎች በመሆናቸው፥ ብዙዎቹ መደበኛ ስልቶች አሏቸው። በእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ ጊዜንና ክስተቶችን ጥርት ባለ ሁኔታ ለመከፈል የተደረገ ጥረት ይታያል። እንዲሁም ደግሞ ለቁጥሮች ተምሳሌታዊ አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ከዚህም የተነሣ ብዙውን ጊዜ የመጨረሻው ውጤት በጥንቃቄ የተደራጁና በቁጥር የሚገለጹ ራእያዊ ስብስቦችን ያመለክታል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ስብስቦች በአንድ ላይ ሲደረጉ እያንዳንዱ የተለያየ ምስል የቀድሞውን ዱካ የግድ እንደሚከተል ሳያሳዩ አንድን ነገር (ለምሳሌ ፍርድ) ይገልጻሉ።

የዮሐንስ ራእይ ከእነዚህ የራእያዊ ጽሑፍ መለያ ባሕርያት የማያሟላው አንዱን ብቻ ነው። ይህ አንድ ልዩነት በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በአንዳንድ መንገዶች የራሱን ዓለም እንዲመሠርት አድርጎታል። ይኸውም ራእይ በሌላ ሰው ስም ያልተጻፈ መሆኑ ነው። ዮሐንስ እዚህ ላይ የተለመደውን ፎርሙላ መከተሉ ጠቃሚ አልመሰለውም። ለአንባቢዎቹ ራሱን የገለጸ ሲሆን፥ በሰባቱ ደብዳቤዎች አማካኝነት (ምዕ. 2–3) በዘመኑ ለነበሩትና አብረውት መከራ ለተቀበሉት የትንቢት እስያ አብያተ ክርስቲያናት ተናግሯል። በተጨማሪም፥ «ጊዜው ስለደረሰ፥ የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው» የሚል መልእክት ከጌታ ዘንድ ተሰጥቶታል (ራእይ 22፡10)።

### የዮሐንስ ራእይ እንደ ትንቢት

የዮሐንስ ራእይ በሌላ ሰው ስም ያልተጻፈበት ዋናው ምክንያት ምናልባትም የመጨረሻው ዘመን ቀድሞውኑ እንደ ደረሰና ዳሩ ግን ገና እንዳልተፈጸመ ከመገንዘቡ የመነጨ ሳይሆን አይቀርም። (የምዕራፍ 7ን የመጨረሻ ክፍል ተመልከት።) ዮሐንስ እንደ አይሁዳውያን ቅድመ ዝሪያዎቹ ዝም ብሎ ፍጻሜውን በመጠባበቅ ላይ አልነበረም። በክርስቶስ መምጣት የፍጻሜው ዘመን እንደ ተጀመረ ያውቅ ነበር። ለዚህ ግንዛቤ ዋንኛው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ነው። ሌሎች የራእያዊ ጽሑፍ ጸሐፊዎች ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ነቢያት ስም ተጠቅመው የጻፉት «መንፈስ ቅዱስ በጠፋበት» ዘመን እየኖሩ፥ መንፈስ ቅዱስ የሚኖርበትን መጭ ዘመን ይጠባበቁ ስለነበር ነው። ስለሆነም፥ እነርሱ የኖሩት ትንቢት ባቆመበት ዘመን ነበር። ዮሐንስ ግን የአዲሱ ዘመን አገልጋይ ነበር። ያየውን እንዲጽፍ በተነገረው ጊዜ «በመንፈስ» ነበር (1፡10–11)። መጽሐፉን «ይህ ትንቢት» ብሎ

ሲጠራው (1፡3፤ 22፡18–19)፥ ይህም እርሱና አብያተ ክርስቲያናት መከራ የሚቀበሉለት «የክርስቶስ ምስክር» (1፡9፤ 20፡4)፥ «የትንቢት መንፈስ» (19፡10) እንደሆነ ገልጾአል። ይህ ምናልባትም ክርስቶስ የመሰከረለትና ዮሐንስና አብያተ ክርስቲያናት እውነትነቱን ያጠናከሩለት የክርስቶስ መልእክት የትንቢት መንፈስ እንደመጣ የሚያስረዱ መሆናቸውን የሚገልጽ ይሆናል።

ስለሆነም፥ የዮሐንስን ራእይ የተለየ የሚያደርገው እነዚህ ራእያዊ ጽሑፍና ትንቢታዊ አላባውያን ተዋህደው የሚገኙበት መሆናቸው ነው። በአንድ በኩል መጽሐፉ ብዙ የራእያዊ ጽሑፍ አላባውያንን ይዞ ይገኛል። ራእይ ስደት የወለደው መጽሐፍ ሲሆን፥ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ ድል ስለሚነሡበት የመጨረሻው ዘመን ይናገራል። በተጨማሪም፥ በተምሳሌቶችና በቁጥሮች የበለጸገ ምሥጢራዊ መልእክት የሚያስተላለፍና በጥንቃቄ የተዘጋጀ ሥነ ጽሑፍ ነው።

በሌላ በኩል፥ ዮሐንስ ይህ ራእያዊ ጽሑፍ ለቤተ ክርስቲያን የተላከ ትንቢታዊ ቃል እንደሆነ በግልጽ ይናገራል። የእርሱ መጽሐፍ እግዚአብሔር በወቅቱ ለነበሩበት ሁኔታ የላከው ቃል እንጂ፥ ለወደፊት ታትሞ የሚቆይ አልነበረም። ትንቢት በቀዳማይነት የወደፊትን ክስተት እንደማያመለክትና በዘመኑ ለሚኖሩ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል በማድረሱ ላይ እንደሚያተኩር ከምዕራፍ 10 ገለጻ ታስታውሳለህ። በዘመኑ ለሚኖሩ አማኞች የሚመጣውም የትንቢት መልእክት ብዙውን ጊዜ የፍርድ ወይም የደኅንነት ይዘት ይኖረዋል። በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ይህንኑ ይዘት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ከተላኩት መልእክቶች ልንመለከት እንችላለን። ስለሆነም፥ ይህ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ማብቂያ አካባቢ ከውጭ ስደትን እየተቀበሉ በውስጣቸው ደግሞ በመበስበስ ላይ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የተላከ የእግዚአብሔር ትንቢታዊ መልእክት ነበር።

## *የዮሐንስ ራእይ እንደ መልእክት*

በመጨረሻም፥ ይህ የራእያዊ ጽሑፍና የትንቢት ውህደት፥ በመልእክት/በደብዳቤ ቅርጽ እንደቀረበ መመልከቱ ጠቃሚ ነው። እንደ 1፡4–7 እና 22፡21 ያሉትን የራእይ ክፍሎች ብታነብ፥ የመልእክት ባሕርያት እንዳሉት ትገነዘባለህ። በተጨማሪም፥ ዮሐንስ ለተደራሲያኑ የሚጽፈው በአንደኛ መደብ (እኔ) እና በሁለተኛ መደብ (እናንተ) ነው። ስለሆነም ራእይ፥ ዮሐንስ ለሰባቱ የትንሹ እስያ፥ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በደብዳቤ መልክ የላከው ጽሑፍ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ይህ ጠቃሚ የሚሆነው እንደ ሌሎች መልእክቶች ሁሉ በራእይም ውስጥ ለመጽሐፉ መጻፍ አስገዳጆች ሆነው የገቡ ሁኔታዎች መኖራቸው ነው (ምዕራፍ 3ን ተመልከት።) በከፊል መጽሐፉ የተጻፈበት ምክንያት ምናልባት በተላከላቸው የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ ይሆናል። ስለሆነም፥ መጽሐፉን ለመተርጎም የመጀመሪያ ታሪካዊ ዓውዱን መገንዘብ አለብን።

## የሐቲት አስፈላጊነት

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አሥራ ሁለት ምዕራፎችን ያህል ከተጓዝን በኋላ አሁንም ስለ ሐቲት አስፈላጊነት መነጋገራችን እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ሰዎች ለራእይ መጽሐፍ ተገቢ ያልሆነና ግምታዊ ትርጉም እንዲሰጡ ያደረጋቸው ትክክለኛ ሐቲታዊ መርሆችን አለመያዛቸው ነበር። ስለሆነም፥ በዚህ ስፍራ ልናደርግ የምንፈልገው ራእይን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከምዕራፍ 3 ጀምሮ የተመለከትናቸውን አንዳንድ መሠረታዊ ሐቲታዊ መርሆች መድገም ይሆናል።

1. የራእይ ሐቲት የመጀመሪያው ተግባር የደራሲውንና የመንፈስ ቅዱስን ፍላጎት መመርመር ይሆናል። እንደ ሌሎች መልእክቶች ሁሉ፥ *የራእይ ቀዳማዊ ፍች ዮሐንስ ሊያስተላልፍ የፈለገውና ተደራሲያኑም የተረዱት ሊሆን ይገባል።* ከእኛ የተሻለ ሊጠቀሙ የሚችሉት ከራሳቸው ታሪካዊ ዓውድ (ቀድሞውኑ መጽሐፉ እንዲጻፍ ካደረገው) ጋር ባላቸው ቅርበትና ለራእያዊ ጽሑፍ ቅርጾችና ምስሎች እንግዳ ባለመሆናቸው ምክንያት ነው።

2. ራእይ ትንቢታዊ መጽሐፍ በመሆኑ፥ ሁለተኛ ፍች ሊኖረው እንደሚችል መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ይህም በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ የተላለፈ ሆኖ በደራሲው ወይም በአንባቢዎቹ በሙላት ያልተጤነ ሊሆን ይችላል። ይሁንና፥ እንዲህ ዓይነቱ ሁለተኛ ፍች ከሐቲት አልፎ በአፈታት ጥበብ አካባቢ የሚገኝ ነው። ስለሆነም፥ በዚህ ስፍራ የሐቲት ተግባር ዮሐንስ የመጀመሪያ ተደራሲያኑ እንዲሰሙና እንዲገነዘቡ የፈለገው ምን እንደነበር መመርመር ይሆናል።

3. በራእይ ሐቲት ውስጥ በተለይ «የመጽሐፍ ቅዱስን» ምስያ ከሚገባው በላይ ላለመጠቀም መጠንቀቅ ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምስያ ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በመጽሐፍ ቅዱስ መተርጎም አለብን ማለት ነው። ይህንን አቋም የወሰድነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑና ዋንኛ ምንጫቸውም እግዚአብሔር እንደሆነ በማመናችን ነው። ይህ ሲባል

ግን ራእይን ለመተርጎም ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን እንደ ሥነ አፈታታዊ ቁልፎች ልንጠቀምባቸው ይገባል ማለት አይደለም።

ስለሆነም፥ ዮሐንስ ከዳንኤል ወይም ሕዝቅኤል በተለየ መንገድ ምስሎችን እንዴት እንደሚጠቀም፥ ወይም የሌሎች መጻሕፍትን ራእያዊ ምስያዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን አንዳንድ የአተረጓጎም ምሁራን እንደሚያደርጉት የዮሐንስ አንባብያን ማቴዎስን ወይም 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄን ያነበቡ በመሆናቸው፥ ከዚሁ ንባባቸው ዮሐንስ የሚያስተላልፈውን መልእክት ለመረዳት የሚያስችል ቁልፍ አግኝተው ነበር ወደሚል ግምት መድረሱ ተገቢ አይሆንም። ስለሆነም፥ *የዮሐንስ ራእይን ለመተርጎም የምንጠቀምበት የትኛውም ቁልፍ ከራሱ ከራእዩ ወይም ከመጀመሪያዎቹ ተደራሲያን ታሪካዊ ዓውድ መፍለቅ ይኖርበታል።*

4. ከመጽሐፉ ራእያዊና ትንቢታዊ ባሕርይ ሳቢያ በሐቲታዊ ደረጃ በተለይም ምስሉን በተመለከተ አንዳንድ ተጨማሪ ችግሮች አሉ። ለዚህ የቀረቡት አንዳንድ አሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡–

ሀ. ራእይን ለማስገኘት ያገለገሉትን የበለጸጉ አሳቦች ማጤኑ አስፈላጊ ነው። የእነዚህ አሳቦችና ምስሎች ዋንኛው ምንጭ የብሉይ ኪዳን ቢሆንም፥ ዮሐንስ ምስሎችን ከራእያዊ ጽሑፎችና አንዳንድ ጥንታዊ አፈታሪኮችም ለመጽሐፉ እንደሚስማሙ አድርጎ ተጠቅሟል። ነገር ግን እነዚህ ምስሎች በራእይ ውስጥ ያገለገሉት በሌሎች ምንጮቻቸው ውስጥ የነበሯቸውን ፍችዎች ይዘው አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ተውጣጥተውና ተለውጠው ይህንኑ «አዲስ ራእይ» ለመፍጠር አገልግለዋል።

ለ. የራእያዊ ጽሑፍ ምስሎች የተለያዩ ዓይነቶች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በአሜሪካ ፖለቲካዊ ካርቱኖች ውስጥ እንደሚታዩ አህዮችና ዝሆኖች ቋሚዎች ናቸው። ለምሳሌ፥ ከባሕር የወጣው አውሬ የግለሰብ ገዥ ሳይሆን የዓለም መንግሥት ምስል ይመስላል። በሌላ በኩል፥ አንዳንድ ምስሎች ተለዋዋጭ ናቸው። የይሁዳ ነገድ «አንበሳ» (በራእይ ውስጥ የተጠቀሰው ብቸኛው አንበሳ) «በግ» ሆኖ እናገኘዋለን (ራእይ 5፡5–6)። በምዕራፍ 12 ውስጥ የተጠቀሰችው ሴት አዎንታዊ ምስል ሲኖራት፥ የምዕራፍ 17ቷ ሴት ግን ክፉ ሴት ሆና ተስላለች።

እንደዚሁም፥ አንዳንድ ምስሎች የተወሰኑ ነገሮችን ያመለክታሉ። በ1፡12–20 የሚገኙ ሰባቱ መቅረዞች ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ፥ በምዕራፍ ፡ 12 ላይ የቀረበው ዘንዶ ሰይጣን እንደሆነ ተመልክቷል። በሌላ በኩል፥ ብዙዎቹ ምስሎች ጠቅለል ያሉ ናቸው።

ለምሳሌ፥ በምዕራፍ 6 ውስጥ የሚገኙት አራት ፈረሰኞች የትኛውንም ውስን ወረራ፥ ጦርነት፥ ረሃብና ሞት የሚያመለክቱ ሳይሆኑ፥ የሰው ልጅ ውድቀት የቤተ ክርስቲያን ሥቃይ ምክንያቶች እንደሆኑ (6፡9–11) እና የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚያስከትሉ የሚያስረዱ ይመስላሉ (6፡12–17)።

ይህን ሁሉ ያልነው ምስሎች የሐቲታዊ ተግባር እጅግ አስቸጋሪ ክፍሎች መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። ስለሆነም፥ ሌሎች ሁለት ነጥቦችን ለማከል እንፈልጋለን።

*ሐ. ዮሐንስ ራሱ ምስሎቹን በሚተረጉምበት ጊዜ እነዚህ ምስሎች በጥብቅ ተይዘው ሌሎችን ለመገንዘብ እንደ መነሻ ነጥብ ሊያገለግሉ ይገባል።* በዚህ ዓይነት ዮሐንስ የተረጎማቸው ምስላዊ ስድስት ምስሎች አሉ። የሰው ልጅ የሚመስለው (1፡17–18) ክርስቶስ ሲሆን፥ እርሱም ሞቶ በመነሣት ለዘላለም የሚኖር ነው። የወርቅ መቅረዞቹ (1፡20) ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ይወክላሉ። ሰባቱ ከዋክብት (1፡20) ሰባቱ መላእክት ወይም የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች ናቸው። (የሚያሳዝነው ይህም ራሱ ምስል ሊሆን ከሚችለው መልአክ የተነሣ ግልጽ አይደለም።) ታላቁ ዘንዶ (12፡9) ሰይጣን ነው። ሰባቱ ራሶች (17፡9) ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራሮች ናቸው። (ይህ ምስል ሰባት ነገሥታትንም ስለሚጨምር ትርጉሙ ተለዋዋጭ ይሆናል።) ጋለሞታይቱ (17፡18) ታላቂቱ ከተማ ስትሆን፥ ይህም ሮምን የሚያመለክት መሆኑ አይጠረጠርም።

*መ. ራእዮችን በምልዓት እንጂ አለጎሪያዊ በሆነ መንገድ ዝርዝሮችን መፈለጉ አስፈላጊ አይደለም።* በዚህ ረገድ ራእዮች እንደ መልእክቶች ናቸው። ጠቅላላው ራእይ ለማስተላለፍ የሚፈልገው አንድ መልእክት ነው። ዝርዝሮቹ አንድም (1) አሳቡን ለማጉላት (6፡12–14)፥ ወይም (2) አንባቢዎቹ ምንባቡ የሚገልጻቸውን ጉዳዮች (የማጣቀሻ ነጥቦቹን) እንዳይስቱ አጠቃላዩን ምስል ለማጉላት የሚቀርቡ ናቸው (9፡7–11)። በመሆኑም፥ ፀሐይ እንደ ሸማ ስለ መጠቅለሏና ስለ ከዋክብት መርገፍ የሚገልጸው ዝርዝር አሳብ ጠቅላላውን የመሬት መንቀጥቀጥ ራእይ የበለጠ ከማጉላት ያለፈ የሚያስተላልፈው መልእክት ያለ አይመስልም። ነገር ግን በ9፡7–11 የወርቅ አክሊል ያደረጉ፥ የሰው ፊት ያሏቸውና የሴቶች ረዥም ፀጉር የሚታይባቸው አንበጦች የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ምንባቡ ስለ ምን እንደሚያወራ በሚገነዘቡበት መልኩ ገለጻውን ምሉዕ ያደርገዋል። ይህም ምንባቡ በሮም ግዛት ዳርቻ ስለሚገኙት ጨካኝ ሕዝቦች እንደሚናገር ለመገንዘብ ያስችላቸዋል።

5. የመጨረሻ አሳብ፡ ብዙውን ጊዜ ራእያዊ ጽሑፎች በአጠቃላይና ራእይ በተናጠል ወደፊት ስለሚፈጸሙት ነገሮች ዝርዝርና ቅደም ተከተላዊ መረጃዎችን አይሰጡም። መልእክታቸው ከዚህ ዓይነት አቅጣጫ ወደማለፉ ያዘነብላል። ሰፊው የዮሐንስ መልእክት በአሁኑ ዘመን ከሚታዩት ሁኔታዎች ባሻገር እግዚአብሔር ታሪክንና ቤተ ክርስቲያንን በመቆጣጠር ላይ ነው የሚል ነው። ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን ሥቃይንና ሞትን ብትጋፈጥም፥ በጠላቶቿ ላይ የሚፈርደውና ሕዝቡን የሚያድነው ክርስቶስ ድልን ይሰጣታል። በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ራእዮች ሁሉ ከዚሁ ሰፊ መልእክት አንጻር ሊታዩ ይገባል።

## ታሪካዊ ዓውድ

እንደ ሌሎቹ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች ሁሉ፥ የራእይን ሐቲት ለመሥራት መጀመር የሚኖርብን መልእክቱ በተጻፈበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ መልሰን በማዋቀር ነው። ይህንንም በጥሩ ሁኔታ ለማድረግ በሌላ ስፍራ ያቀረብነውን አሳብ መጠቀም ይኖርብሃል። ሰፊውን ምስል ለማግኘት ጠቅላላውን መጽሐፍ በአንድ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። ሁሉንም ነገር ለመረዳት አትሞክር። ንባብህ ራሱ እንደ አንድ ክስተት ይሁን። መጽሐፉና መልእክቶቹ ስሜትህን እስኪነኩ ድረስ ራእዮቹ እንደ ባሕር ሞገድ ወደ ኋላ እንዲቀለብሱህ አድርግ።

በተጨማሪም፥ በምታነብበት ጊዜ ስለ ደራሲውና ተደራሲያኑ አጭር የአእምሮ ወይም የወረቀት ማስታወሻ ያዝ። አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ መጽሐፉን በማንበብ የዮሐንስ ተደራሲያን የመከራው ተከፋዮች (1፡9) መሆናቸውን የሚገልጹትን ጥቅሶች ሁሉ ለይ። እነዚህ ወሳኝ ታሪካዊ አመልካቾች ናቸው።

ለምሳሌ፥ በሰባቱ ደብዳቤዎች ውስጥ 2፡3፥ 8–9፥ 13፥ 3፡10 እና «ድል ለሚነሣ» የሚለውን የተደጋገመ አሳብ አጢን። አራቱ ፈረሰኞች የሚያስከትሉትን ውድመት ተከትሎ የሚመጣው አምስተኛው ማኅተም (6፡9–11) ስለ «ቃሉ» እና ስለ «ምስክርነታቸው» (ዮሐንስ በፍጥሞ የነበረው ለዚሁ ተግባር ነበር፤ 1፡9) የተገደሉትን ክርስቲያን ሰማዕታት ያሳያል። በ7፡14 ከእንግዲህ ወዲህ መከራን የማይቀበል (7፡16) እጅግ ብዙ ሕዝብ ከታላቁ መከራ ሲመጣ ይታያል። በ12፡11 እና 17 መከራና ሞት ለክርስቶስ ከመመስከር ጋር ተጣምረዋል። ከ13–20 ባሉት ምዕራፎች መከራና ሞት ከአውሬው ጋር ተዛምደው ቀርበዋል (13፡7፡ 14፡9–13፤ 16፡5–6፤ 18፡20፥ 24፤ 19፡2)።

ይህ ጥብጥ ታሪካዊ ዓውዱን ለመረዳት ቁልፍ ሲሆን፥ መጽሐፉ እንዲጻፍ ያስገደደውን ሁኔታና ዓላማዎ ይገልጻል። ዮሐንስ ራሱ

በእምነቱ ምክንያት ታስሮ ነበር። ሌሎችም መከራ በመቀበል ላይ ነበሩ። ከመካከላቸውም አንዱ ለክርስቶስ ምስክርነት ሞቷል (2፡13)። ዮሐንስ በመንፈስ ሆኖ የእነርሱ መከራ አውሬውን ላለማምለክ አማኞች ሁሉ የሚቀበሉት ፈር ቀዳጅ ተግባር መሆኑን ተገነዘበ። በተመሳሳይ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በፊቷ ላለው መከራ ዝግጁ ለመሆኗ እርግጠኛ አልነበረም። ስለሆነም፥ ይህንኑ ትንቢት ሊጽፍ ችሏል።

የመጽሐፉ ዐበይት ጭብጦች ግልጽ ናቸው። ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በመጋጨት ላይ መሆናቸውንና የመጀመሪያው ድል የመንግሥት እንደሚሆን ተገንዝቧል። ስለሆነም፥ ከቤተ ክርስቲያን ጎዳና ላይ መከራና ሞት እንዳለ በመግለጽ ያስጠነቅቃል። ይህም ሁኔታ መልኩን እስኪቀይር ድረስ ወደ ከፋ ደረጃ ይደርስ ነበር (6፡9–11)። በመከራ ጊዜ እምነታቸውን ትተው ለመንግሥት ትእዛዝ እጅ እንዳይሰጡ ሰግቶ ነበር (14፡11–12፤ 21፡7–8)። ነገር ግን ይህ የትንቢት ቃል ማበረታቻም ጭምር ነበር። እግዚአብሔር ሁሉንም በመቆጣጠር ላይ ነውና። ክርስቶስ የታሪክን ቁልፎች ይይዛል፤ አብያተ ክርስቲያናትም በእጁ ውስጥ ናቸው (1፡17–20)። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በሞት መካከልም እንኳ ቢሆን በድል ታልፋለች (12፡11)። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር ይህንን ሥቃይና ሞት ባስከተሉት ሰዎች ላይ ቁጣውን በማዝነብ በታማኝነት ለጻኑት ዘላለማዊ ዕረፍትን ያጎናጽፋል። በዚያ ዓውድ፥ ፍርድ የሚደርስባት የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ጠላት ሮም ነበረች።

ራእይን ለመተርጎም ከሚያስፈልጉት ቁልፎች አንዱ ዮሐንስ በሁለት ቃላት ወይም አሳቦች መካከል የሚያሳያቸው ልዩነቶች መሆናቸውን አስተውል። እነዚህም ሁለት ቃላት *መከራ* እና *ቁጣ* የሚሉ ናቸው። እነዚህን ሁለት ቃላት ቀላቅሎ አንድ ነገር እንደሚያመለክቱ ማሰብ፥ የመልእክቱን አሳብ በከፍተኛ ደረጃ የሚያዛባ መሆኑን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው።

መከራ (ሥቃይና ሞት) ቤተ ክርስቲያን በትዕግሥት እየተቀበለች የነበረችውና ወደፊትም ገና የምትቀበለው ችግር ነበር። በሌላ በኩል፥ የእግዚአብሔር ቁጣ እግዚአብሔር ሕዝቡን በጎዱት ሁሉ ላይ የሚያወርደው ፍርድ ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ በጠላቶቻቸው ላይ እግዚአብሔር የሚያወርደውን ቁጣ እንደማይቀበሉ ከራእይ ዓውድ እንገነዘባለን። ነገር ግን ከጠላቶቻቸው መከራ እንደሚደርስባቸው ግልጽ ነው። ይህ ልዩነት ከቀረው የአዲስ ኪዳን መልእክት ጋር የሚደጋገፍ እንደሆነ እንመለከታለን። ለምሳሌ ያህል፥ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ሰዎች መሰደድና መከራን መቀበል (ታላቅ መከራ የሚል አሳብ የሚያመለክቱ ተመሳሳይ የዕርዕ ቃላት) የሚመካበትን የ2ኛ

ተሰሎንቄ 1፡3–10 ምንባብ ተመልከት። ነገር ግን እግዚአብሔር የኋላ ኋላ መከራ በሚያሳዩዋቸው ላይ እንደሚፈርድም ገልጾአል።

በተጨማሪም፥ የማኅተም 5 እና 6 መከፈት (6፡9–17) በመጽሐፉ ውስጥ ሁለት ዋንኛ ጥያቄዎችን እንደሚያስነሣም ልብ በል። በማኅተም 5 ክርስቲያን ሰማዕታት፥ «ሁሉን የምትገዛ--- ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ አትፈርድም? እስከ መቼስ ደማችንን በምድር በሚኖሩት ላይ አትበቀልም?» ሲሉ ይጮኻሉ። መልሱ ሁለት እጥፍ ነው፤ (1) ገና ሌሎች በሰማዕትነት የሚያልፉ ስላሉ ትንሽ መጠበቅ ነበረባቸው። (2) 6ኛው ማኅተም እንደሚያመለክተው፥ ፍርድ እንደሚሰጥ የተረጋገጠ ነው።

በማኅተም 6 የእግዚአብሔር ፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ፍርዱን የሚቀበሉት፥ «ማንስ ሊቆም ይችላል?» ሲሉ ጮኹ። ለዚህ ጥያቄ መልሱ በምዕራፍ 7 ውስጥ ቀርቧል። እግዚአብሔር ያተማቸው፥ ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው ያነጹት ይቆማሉ።

## ሥነ ጽሑፋዊ ዓውድ

በዮሐንስ ራእይ ውስጥ የትኞቹንም ውስን ራእዮች ለመረዳት ከዳራና ከምስሎች ፍች (የይዘት ጥያቄዎች) ጋር መታገል ብቻ ሳይሆን፥ አንዱ ራእይ በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ እንዴት እንደሚያገለግል መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ፥ ራእይ ከትንቢት ይልቅ ወደ መልእክትነቱ ያደላል። ትንቢቶች ሁልጊዜም እርስ በርሳቸው ምን ዓይነት ተግባራዊ ዓላማ እንዳላቸው የማይገልጹ የትንቢታዊ መልእክቶች ስብስብ ናቸው። በመልእክቶች ውስጥ ግን እያንዳንዱ አንቀጽ ለጠቅላላው አሳብ የማነጫ ድንጋይ በመሆኑ፥ ከአንቀጾች አኳያ ማሰብን ይጠይቃል። ራእይም እንዲሁ ነው። መጽሐፉ በጥበባዊ ብልሃት የተዋቀረ አንድ ወጥ ሲሆን፥ እያንዳንዱ ራእይ የዚያ ወጥ አካል ነው።

ራእይን የሚመስል መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለሌለ፥ አንድ ወይም ሁለት ሞዴሎችን ከመስጠት ይልቅ ከዳር እስከ ዳር ልንመራህ እንሻለን። እዚህ ላይ መሠረታዊ መዋቅሩ ግልጽ ስለሆነ የማያከራክር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ልዩነቶች የሚከሰቱት በመዋቅሩ አተረጓጎም ላይ ነው።

መጽሐፉ የቀረበው የመጀመሪያዎቹ ትእይንቶች መድረኩንና ገጸ ባሕርያቱን እንደሚያስተዋውቁበትና የኋለኞቹ ትእይንቶች ደግሞ ሤራውን በትክክል ለመከተል የመጀመሪያዎቹን ትእይንቶች እንደሚፈልጉበት ታላቅ ተውኔት ነው።

ከምዕራፍ 1–3 መድረኩን በመክፈት ከአብዛኞቹ ጠቃሚ «ገጸ ባሕርያት» ጋር ያስተዋውቀናል። መጀመሪያ፥ ታሪኩን እስከ መጨረሻው የሚተርከው ዮሐንስ አለ (1፡1–11)። ዮሐንስ በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት የተሰደደ ክርስቲያን ሲሆን፥ በዚያን ጊዜ የነበረው ስደት ወደፊት ለሚመጣው ጥርጊያ መንገድ ብቻ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ትንቢታዊ መረዳት ነበረው።

ሁለተኛ፥ ዮሐንስ በሚያስደንቁ ምስሎች አማካይነት የገለጸው ክርስቶስ አለ (1፡12–20)። ከእነዚህ ምስሎች አንዳንዶቹ የተወሰዱት ከዳንኤል ምዕራፍ 10 ሲሆን፥ ክርስቶስ የታሪክና የቤተ ክርስቲያን ጌታ መሆኑን ያስረዳሉ። የሞትና የሲኦል ቁልፍ የሚገኘው በክርስቶስ እጅ ብቻ ስለሆነ፥ በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች በስደት ውስጥ ማለፋቸው እግዚአብሔር ዓለምን ለመቆጣጠር አለመቻሉን የሚያመለክት አልነበረም።

ሦስተኛ፥ ቤተ ክርስቲያንም ተጠቅሳለች (2፡1–3፡22)። ዮሐንስ ለሰባት እውነተኛና ወኪል አብያተ ክርስቲያናት በጻፋቸው ደብዳቤዎች፥ ቤተ ክርስቲያንን ያበረታታል፤ ይወቅሳታልም። ቤተ ክርስቲያን በስደት ውስጥ የነበረች ስትሆን፥ ገና ከዚያ የከፋ እንደሚመጣም ተመልክቷል። ነገር ግን ደኅንነቷን የሚፈታተኑ ሌሎች ውስጣዊ ችግሮችም ነበሩ። ፈተናውን ያሸነፉ በመጨረሻው እንደሚከብሩ ተገልጾአል።

ምዕራፍ 4–5ም መድረኩን ለማስተዋወቅ ያገለግላሉ። እጅግ በሚማርኩ የአምልኮና የምስጋና ራእዮች አማካኝነት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሉዓላዊ ግርማው እንደሚገዛ እንድትገነዘብ ተደርጓል (ምዕ. 4)። የሚያስብልኝ አምላክ አለ ወይ? በሚል ለሚፍገመገሙ ክርስቲያኖች፥ ዮሐንስ የእግዚአብሔር «አንበሳ» ራሱ የሰውን ልጅ በመከራ ነፃ ያወጣ «በግ» እንደሆነ ያረጋግጣል (ምዕ. 5)።

ከምዕራፍ 6–7 ድራማው በትክክል ይጀመራል። በመጽሐፉ ሁሉ ውስጥ ሦስት ጊዜ ራእዮች በጥንቃቄ በተዋቀሩ የሰባት ቡድኖች ቀርበዋል (ምዕ. 6–7፥ 8–11፥ 15–16)። በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራት ነገሮች አንድን ምስል ለመፍጠር አብረው ይሰበዛሉ። በ6–7 እና 8–11 ደግሞ የመጨረሻዎቹ ሁለት ነገሮችም የሌላ እውነታ ሁለት ገጽታዎች ለመሥራት ለመፍጠር አገልግለዋል። እነዚህም ሰባተኛው ክስተት ከመምጣቱ በፊት በሁለት ራእዮች ጣልቃ ገብነት ተስተጓጉለዋል። ከ15–16 የመጨረሻዎቹ ሦስት ቡድኖች ያለ ጣልቃ ገብ ራእዮች ይቀርባሉ። ይህ ከ6–7 እንዴት እንደሚሠራ ተመልከት።

1. ነጭ ፈረሰኛ = ወረራ

2. ቀይ ፈረሰኛ = ጦርነት

3. ጥቁር ፈረሰኛ = ረሃብ

4. ውይብ ፈረሰኛ = ሞት

5. «ምን ያህል?» የሚለው የሰማዕታት ጩኸት

6. «ማን ሊቆም ይችላል?» የሚለው የምድር መንቀጥቀጥ (የእግዚአብሔር ፍርድ)

   ሀ. 144,000 ታትመዋል

   ለ. እጅግ ብዙ ሕዝብ

7. የእግዚአብሔር ቁጣ፡ የምዕራፍ 8–11 ሰባቱ መለከቶች

ምዕራፍ 8–11 የእግዚአብሔርን ፍርድ ይዘት ይገልጻል። የመጀመሪያዎቹ አራት መለከቶች እነዚያ የፍርዱ አካላት ወደፊት ከፍተኛ ችግር እንደሚያስከትሉ ያስረዳሉ። መለከት 5 እና 6 ፍርዱ ከጨካኝ ሕዝቦችና ከታላቅ ጦርነት እንደሚመጣም ያመለክታሉ። ቢሞቱም እንኳ እግዚአብሔር በምስክርነታቸው እንደከበረ ከሚያሳየው ጣልቃ ገብ ራእይ በኋላ ሰባተኛው መለከት ፍጻሜውን ያውጃል፤ «የዓለም መንግሥት፤ የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት ሆነች።»

ስለሆነም፥ በቤተ ክርስቲያን መከራና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በሚሰጠው ፍርድ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር የመጨረሻ ድል ነሺነት እንደርሳለን። ነገር ግን ራእዮቹ በዚህ አላበቁም። ከምዕራፍ 8–11 ትልቅ ምስል ተሰጥቶን ነበር። ከ12–22 ስለ ፍርዱና ድል ነሺነቱ ዝርዝር ጉዳዮችን ያቀርባሉ። የራእይ መጽሐፍ አቀራረብ "Sistine Chapel" የተባለውን የሚካኤል አንጀሎን ሥዕል ይመስላል። መጀመሪያ በዚህ ቻፕል ጠቅላላ ይዘት እንደመምና ቀስ በቀስ ዝርዝር ክፍሎቹን መገንዘብ እንጀምራለን።

ምዕራፍ 12 ለመጽሐፉ ሥነ መለኮታዊ ቁልፍ ነው። ሰይጣን ክርስቶስን ለማጥፋት ሞክሮ መሸነፉ በሁለት ራእዮች ተነግሮናል። ስለሆነም ቀድሞ/ገና በሚለው ተደጋጋሚ የአዲስ ኪዳን መዋቅር፥ ሰይጣን እንደ ተሸነፈ ጠላት (ቀድሞ) እና ዳሩ ግን ገና ወደ ፍጻሜው እንዳልደረሰ ጠላት ሆኖ ተመልክቷል። ስለሆነም፥ ደኅንነት ስለመጣ የደስታ ዓውድ ይታያል። ነገር ግን ሰይጣን ጊዜው እንደ ደረሰ አውቆ

በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የበቀል እርምጃ እየወሰደ በመሆኑ ዋይታም አለ።

ስለሆነም በምዕራፍ 13–14 ይኸው በቀል በዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው፥ የሮም መንግሥት ነገሥታት ሃይማኖታዊ ስግደትን በመጠየቃቸው ነበር። ነገር ግን መንግሥቱም ሆነ ነገሥታቱ ለውድቀት ተዳርገዋል (ምዕ. 15–16)። መጽሐፉ እንደ «የሁለት ከተሞች ወግ» ይቋጫል (ምዕ. 17–22)። ምድራዊቱ ከተማ (ሮም) የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማውገዟ ተኮንናለች። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ለዘላለም ስለሚኖሩባት የእግዚአብሔር ከተማ በሚናገረው ታሪክ ይተካል።

በዚህ አጠቃላይ መዋቅር ውስጥ አያሌ ራእዮች ከፍተኛ ችግሮችን ያስከትላሉ። ይህም ከይዘታቸው ፍችና በዓውድ ውስጥ ከሚያበረክቱት አገልግሎት ጋር የተያያዘ ነው። ለእነዚህ ጥያቄዎች ምርጥ ከሚባሉ የማብራሪያ መጻሕፍት አንዱን ብታገኝ መልካም ነው። (ለምሳሌ፣ «Beasley-Mauray or Mounce;» ተጨማሪ አሳቦች የቀረቡበትን የዚህን መጽሐፍ ክፍል ተመልከት።)

## ሥነ አፈታታዊ ጥያቄዎች

የዮሐንስ ራእይ ሥነ አፈታታዊ ጥያቄዎች በምዕራፍ 10 ውስጥ ከተመለከትናቸው የትንቢት መጻሕፍት ጋር አንድ ዓይነት ናቸው። እንደ ሌሎቹ የሥነ ጽሑፍ ቅርጾች ሁሉ፥ ለእኛ የሚመጣው የእግዚአብሔር ቃል ለእነርሱ የሰጣቸው ነው። ከሌሎች የሥነ ጽሑፍ ቅርጾች በተቃራኒ ግን የትንቢት መጻሕፍትና ነቢያት ለእነርሱም ገና ተፈጻሚነት ስላላገኙት ነገሮች ይናገራሉ።

ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ለእነርሱ ገና ወደፊት ይፈጸም የነበረው ክስተት አሁን እኛ ዘወር ብለን ስንመለከት ተፈጽሞ እናገኘዋለን። ስለሆነም፥ ልክ ኤርምያስ እንደተናገረው የይሁዳ ሕዝብ ወደ ምርኮ ከሄደ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሷል። ዮሐንስ እንደተነበየው፥ የሮም መንግሥትም በጊዜያዊ ፍርድ ተቀጥቷል።

ለእንደዚህ ዓይነት እውነታዎች ሥነ አፈታታዊ ችግሮች ያንን ያህል የገዘፉ አይደሉም። አሁንም የፍርድ ምክንያቶችን እንደ እግዚአብሔር ቃል ልንሰማቸው እንችላለን። «ለአንድ ጥንድ ጫማ ድሆችን የሚረግጡትን» እግዚአብሔር ሁልጊዜም እንደሚቀጣ በአግባቡ ልንገነዘብ እንደምንችል ሁሉ፥ እንደ ሮም ክርስቲያኖችን በገደሉት አገሮችም ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚደርስ ልንረዳ እንችላለን።

በተጨማሪም፥ ደቀ መዝሙርነት የመስቀሉን መንገድ እንደሚከተል የሚያስረዳውን የእግዚአብሔር ቃል ልንሰማ እንችላለን። ይህም

እግዚአብሔር ከመከራና ሞት ነፃ እንደምንሆን ሳይሆን በዚያ ውስጥ ድል እንደሚሰጠን የተናገረ መሆኑን ያስገነዝበናል። ሉተር በትክክል እንደገለጸው፥ «የጨለማው ንጉሥ ቢቆጣም አንፈራውም... ሰውነትን ሊገድሉ ቢችሉም፥ የእግዚአብሔር እውነት ግን ይኖራል – መንግሥቱ ዘላለማዊ ነው።»

ስለሆነም፥ ራእይ በቻይናም ይሁን በካምፖቺያ በዩጋንዳም ሆነ በየትኛው የዓለም ክፍል መከራ የሚቀበሉትን ክርስቲያኖች ለማጽናናትና ለማበረታታት የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ነው። እግዚአብሔር ነገሮችን በመቆጣጠር ላይ ነው። የልጁን ጥሪት ስለተመለከተ፥ በዚህ ይረካል።

ይህ ሁሉ በሁሉም ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተደጋጋሚ ሊደመጥ የሚገባው እውነት ነው። ይህንን ቃል መሳት ማለት ደግሞ የጠቅላላውን መጽሐፍ አሳብ መሳት ማለት ነው።

ነገር ግን ሥነ አፈታታዊ ችግሮቻችን የሚመነጩት የመጽሐፉ መልእክት የሆነውን የማስጠንቀቂያና የማጽናኛ ቃል ከመስማት አይደለም። ችግሮቻችን ከሌላው የትንቢት ገጽታ ጋር የተያያዙ ናቸው። ይኸውም «ጊዜያዊው» ቃል ብዙውን ጊዜ ከመጨረሻዎቹ የፍጻሜ እውነታዎች ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው። (ገጽ 190 ተመልከት።) ይህ በተለይ በራእይ ውስጥ እውነት ነው። በአጠቃላይ ፍጻሜ ውስጥ በምዕራፍ 18 የሮም ውድቀት ቀዳሚ ምዕራፍ ሆኖ ሲቀርብ፥ ብዙ የ«ጊዜያዊ» ፍርድ ቃላትና አሳቦች የመጨረሻውን ፍጻሜ የምስሉ አካል አድርገው ከሚያቀርቡት ነገሮች ጋር ተሳስረዋል። የዚህን እውነታ ማስወገድ የሚቻልበት መንገድ ያለ አይመስልም። ጥያቄው እንግዲህ ምን እናድርግ? የሚል ነው። ቀደም ብለን በምዕራፍ 10 ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሰጥተናል። እዚህ ግን ጥቂት አሳቦችን ብቻ እናቀርባለን።

1. የወደፊት መግለጫዎች፥ መግለጫዎች ብቻ መሆናቸውን ልብ እንበል። መግለጫዎች ስለ እውነታ ቢናገሩም፥ እውነታዎች አይደሉም። ወይም ደግሞ የሁሉም መግለጫ ዝርዝሮች የግድ በሆነ ውስን መንገድ መፈጸም የለባቸውም። ስለሆነም፥ የመጀመሪያዎቹ አራት መለከቶች በተፈጥሮ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሲያውጁ፥ የእነዚህን ነገሮች ቀጥተኛ ፍጻሜ መጠባበቅ የለብንም።

2. በቀዳሚነት የእግዚአብሔርን ፍርድ እርግጠኛነት ለመግለጽ የቀረቡ አንዳንድ አሳቦች «አሁኑኑ» እንደሚፈጸሙ አድርገን መተርጎም የለብንም። ይህ በተለይ ከውስን አመለካከታችን አንጻር ሊደረግ የማይገባው ነው። ስለሆነም ሰይጣን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ

ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከት ለመፍጠር ወደ ምድር ሲጣል፥ ጊዜው አጭር እንደሆነ ያውቅ ነበር። ነገር ግን «አጭር» የሚለው ቃል ድርጊቱ ወዲያውኑ እንደሚፈጸም ሳይሆን የተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዳለው የሚያመለክት ነው። እንዲያውም ለዘላለም «የሚታሰርበት» ዘመን የሚመጣ ቢሆንም፥ ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን የሚያውቅ ማንም የለም።

3. «ጊዜያዊው» ከ«ፍጻሜው» ጋር በቅርብ የተገናኘባቸው መግለጫዎች ሁለቱም በአንድ ጊዜ ይፈጸማሉ ወደሚል አተረጓጎም ሊመሩን አይገባም። የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ወደዚህ ድምዳሜ ቢደርሱም እንኳ፥ ይህንኑ ከማድረግ መታቀብ ይኖርብናል (ገጽ 190 ተመልከት።) የፍርድና ደኅንነት «ፍጻሜያዊ» አቅጣጫ ስለ ብዙዎቹ መግለጫዎች «ገና-ወደፊት» ስለሚለው አቅጣጫ ንቁዎች ሊያደርገን ይገባል። በሌላ በኩል፥ ይህንኑ «ገና-ወደፊት» እንዴት እንደምንገነዘብ የሚረዱን የተወሰኑ አላባውያን የሉም። ልናደርግ የማይገባን ነገር ቢኖር በዘመናችን የሚገኙ ክስተቶችን በራእይ መግለጫዎች ውስጥ ለማስገባት ግምታዊ ስሌቶችን በማካሄድ ብዙ ጊዜ ማጥፋት እንደሌለብን ነው። መጽሐፉ የተጻፈው ስለ ቀይ ቻይና መኖር ወይም ስለ ታሪክ ፍጻሜ ቀጥተኛ ዝርዝሮችን ለመስጠት አይደለም።

4. ምንም እንኳ ገና ወደፊት የሚፈጸሙ ብዙ (ሁለተኛ) ካልዐዊ የመግለጫዎቹ አካላት ሊኖሩ ቢችሉም፥ እነዚህን እንዴት እንደምንለይ የሚያስችሉ ቁልፎች አልተሰጡንም። በዚህ ረገድ አዲስ ኪዳን ራሱ የተወሰነ አደናጋሪነት ይታይበታል። ለምሳሌ፥ ስለ ሐሳዊ መሢሕ መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ (2ኛ ተሰ. 2፡3-4) የራሱ ማንነት ተሰጥቶታል። በራእይ 13-14 ውስጥ በሮም ንጉሥ መልክ ይገለጣል። በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ ግን ይህ ሁሉ ዳግም ትርጓሜ ተሰጥቶት በወቅቱ ቤተ ክርስቲያንን በመውረር ላይ የነበሩትን የኖስቲክስ ትምህርት ተከታዮች እንዲያመለክት ተደርጓል። እንግዲህ፥ ከራሳችን የወደፊት ትንበያ አኳያ ይህንን ሰው የምንገነዘበው እንዴት ነው?

በታሪክ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የሐሳዊ መሢሕ ባሕርይ ያላቸውን ብዙ መሪዎች አይታለች። ሂትለርና ኢዲ አሚን ከእነዚህ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ መልኩ ካየን ብዙ ሐሳዊ መሢሖች መምጣታቸውን ይቀጥላሉ (1ኛ ዮሐ. 2፡18)። ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን የሚገለጠው ዓለም አቀፋዊ መሪስ ጉዳይ? ራእይ 13-14 እንዲህ ዓይነት ሰው እንደሚመጣ ያሳያል? የእኛ አመለካከት፥ የግድ እንደዚህ ላይሆን ይችላል የሚል ነው። ነገር ግን ሊሆን እንደሚችልም

እናስባለን። በዚህ ጉዳይ ላይ እርግጠኞች እንዳንሆን ያደረገን ራሱ አዲስ ኪዳን አሻሚ ትርጉም ያለው መልእክት መስጠቱ ነው።

5. ሙሉ በሙሉ የፍጻሜውን ዘመን የሚያመለክቱ መግለጫዎች በዚያ መልኩ መታየት ይኖርባቸዋል። በዚህ መሠረት፥ የ11፡1–19 እና 19፡1–22፡21 አሳቦች ሙሉ በሙሉ የመጨረሻውን ዘመን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህንን ወደፊት እንደሚፈጸም የእግዚአብሔር ቃል ልናስተናግደው ይገባል። ነገር ግን እነዚህም እንኳ እግዚአብሔር በራሱ መንገድና ጊዜ የሚፈጽማቸው መግለጫዎች ናቸው። እንዲሁም ደግሞ በክፍሉ ውስጥ ከቀረበው በላቀ ሁኔታ እንደሚፈጸሙ እናምናለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመክፈቻ ክፍሎች ስለ እግዚአብሔርና ፍጥረት እንደሚናገሩ ሁሉ፥ የማጠቃለያውም ቃል ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍጻሜ ይናገራል። ዝርዝር ነገሮች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ አስመልክቶ አንዳንድ ነገሮች ግልጽ ባይሆኑልንም እንኳ፥ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜና መንገድ ሁሉንም ፈር እንደሚያስይዝ የሚያጠራጥር አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ እርግጠኝነት ለእነርሱ እንደሆነው ሁሉ እኛንም ሊያስጠነቅቀንና ሊያበረታታን ይገባል።

እርሱ እስኪመጣ ድረስ፥ ወደፊትን በቀደመው ብርሃን እንኖራለን። ይህንንም የምናደርገው ቃሉን በመስማትና በመታዘዝ ነው። ነገር ግን እንደዚህ ዓይነቱ መጽሐፍ የማይፈለግበት ዘመን ይመጣል። «ከእንግዲህ ማንም ሰው ባልንጀራውን፤ ወይም ወንድሙን፤ ሑእግዚአብሔርን ዕወቅመ ብሎ አያስተምርም፤ ከትንሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ ሁሉም እኔን ያውቁኛልና» (ኤር. 31፡34)። እንዲሁም፥ ከዮሐንስ፥ ከመንፈሱና ከሙሽራይቱ ጋር፥ «አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና» እንላለን።

# ተጨማሪ አሳቦች

## የማብራሪያ መጻሕፍት (Commentaries)

## ግምገማና አጠቃቀም

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጥሩ የማብራሪያ መጻሕፍት ለመጠቀም የምትፈልግባቸው ጊዜያት እንደሚኖሩ በተደጋጋሚ መግለጻችን ይታወሳል። ይህንን ማድረጋችንን እንደ ስሕተት አንቆጥረውም። ጥሩ የማብራሪያ መጽሐፍ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልገው እንደ ጥሩ ስብከት፥ ጥሩ የትምህርት ካሴቶች፥ እንደ ጥሩ አማካሪ ነውና።

በዚህ ምዕራፍ ዓላማችን በጣም ቀላል ነው። የአንድን የማብራሪያ መጽሐፍ ሐቲታዊ እሴት እንዴት እንደምትገመግም ጥቂት አሳቦችን ከሰነዘርን በኋላ፥ ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ጥሩ ናቸው የምንላቸውን አንድ ወይም ሁለት የማብራሪያ መጻሕፍት እንጠቁምሃለን። በእርግጥ ሁልጊዜም አዳዲስ ግሩም የማብራሪያ መጻሕፍት እየታተሙ ስለሚወጡ (በውጭ አገሮች በእንግሊዝኛ ቋንቋ)፥ እንዲህ ዓይነቱ ዝርዝር የራሱ ችግሮች እንዳሉት ግልጽ ነው። እኛ የዘረዘርናቸው ይህንን መጽሐፍ በምንጽፍበት ጊዜ ታትመው የወጡትን ብቻ ነው። አዳዲስ የማብራሪያ መጻሕፍት ታትመው በሚወጡበት ጊዜ ራስህ በሚከተሉት መስፈርቶች ልትመዝናቸው ትችላለህ።

## የማብራሪያ መጻሕፍት ግምገማ

ከልብህ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ከሆንህ፥ ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ጥሩ የማብራሪያ መጻሕፍት እንዲኖሩህ ትሻለህ። በእርግጥ በአንድ ጥራዝ ሁሉንም መጽሐፍ ያካተተ አርኪ የማብራሪያ መጽሐፍ ማግኘቱ ያስቸግራል። ባለ አንድ ጥራዝ ማብራሪያዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ራስህ እንድታካሄድ የሰጠንህን ሥራ ለማከናወን የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ታሪካዊ ዓውዱን ይሰጡና የምንባቡን ፍች ከሥነ ጽሑፋዊ ዓውዱ አኳያ ያቀርቡልሃል። ይህ የራሱ ጥቅም ቢኖረውም፥ አብዛኛውን እንደ «Eerdmans's Bible Handbook» በመሳሰሉት ሥራዎች ውስጥ ልታገኝ ትችላለህ። የማብራሪያ መጽሐፍ የሚያስፈልግህ በመሠረቱ ሦስት ነገሮችን ለማድረግ ነው። እነዚህም፥ (1) ስለ ታሪካዊ ዓውድ ምንጮችንና መረጃዎችን ለማግኘት፥ (2) የተለያዩ ይዘቶች ላሏቸው ጥያቄዎች

መልሶችን ለማግኘት፥ እና (3) ለአስቸጋሪ ምንባቦች መረጃዎች ያሏቸውን ፍችዎች ለማግኘት ናቸው።

እንግዲህ፥ አንድ ሰው አንድን የማብራሪያ መጽሐፍ የሚገመግመው እንዴት ነው? በመጀመሪያ ደረጃ፥ ከደራሲው ጋር ባለህ የአመለካከት ተመሳሳይነት ላይ ተመሥርተህ አትገመግምም። የማብራሪያ መጽሐፉ ጥሩ ከሆነና አንተም የራስህን ሐቲት ጥሩ አድርገህ ከሠራህ፥ ብዙውን ጊዜ የአንተና የጥሩ ማብራሪያዎች አሳብ ተመሳሳይ ይሆናል። ነገር ግን የማብራሪያዎቹ ከአንተ አሳብ ጋር መስማማት መሠረታዊ መመዘኛ አይደለም።

በተጨማሪም፥ አንድ የማብራሪያ መጽሐፍ የምትገመግመው አንተን በሳበበት ሁኔታ ላይ ተመሥርተህ አይደለም። ከማብራሪያ መጽሐፍ የሚጠበቀው ዋናው ነገር ሐቲት ነው። ይህም ምንባቡ የሚያስተላልፈውን መልእክት ፍች መግለጹ እንጂ በዘመናችን ምንባቡን የምንሰብከበትን ሁኔታ ማስረዳቱ አይደለም። አንድን ምንባብ እንዴት በአሁኑ ዘመን መጠቀም እንደምትችል ለማወቅ በምትፈልግበት ጊዜ ስለ ስብከት የሚያስረዱ መጻሕፍት ሊጠቅሙህ ይችላሉ። ስላለንበት ዘመን ለማሰብ እንድንችል ሰባኪዎች እንደ መሆናችን እኛም እንደነዚህ ዓይነት መጻሕፍትን እንጠቀማለን። ምንም እንኳ እነዚህ መጻሕፍት አሁንና እዚህ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መጠቀም እንዳለብን ቢያሳዩንም፥ ማብራሪያዎች አይደሉም። በዚህ ስፍራ ለማተኮር የምንፈልገው በእንደዚህ ዓይነት መጻሕፍት ላይ ሳይሆን፥ በሐቲታዊ ማብራሪያዎች ላይ ብቻ ነው።

የአንድን ማብራሪያ ጥሩ መሆን ወይም አለመሆን ለመወሰን ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ቢያንስ ሰባት መመዘኛዎች አሉ። እነዚህ ሁሉ ግን አንድ ዓይነት ወይም እኩል አስፈላጊነት ያላቸው አይደሉም። እነዚህ ሁሉ ግን አንድን ዋንኛ ነጥብ ለማገዝ ተዋህደው ይቀርባሉ። ይኸውም፥ ይህ ማብራሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት እንድትረዳ ያግዝሃል ወይ? የሚል ነጥብ ነው።

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስለ ማብራሪያ ማወቅ የሚኖርብህ መረጃዎች ናቸው።

1. ማብራሪያው ሐቲታዊ ነው? ስብከታዊ ነው? ወይስ ሁለቱንም? ይህ ከላይ የገለጽነው አሳብ ነው። ከማብራሪያ በጥብቅ የምንፈልገው ሐቲትን እንደሆነ አስተውል። መጽሐፉ ከሐቲት በተጨማሪ ሥነ አፈታታዊ አሳቦችን የሚሰነዝር ከሆነም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ነገር

ግን በዋንኛነት የሚያስፈልግህ ለይዘት ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት ነው። የይዘት ጥያቄዎች ደግሞ በቀዳሚነት ሐቲታዊ ናቸው።

2. ማብራሪያው የተመሠረተው በዕርዕ ወይም ዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው ወይስ በእንግሊዝኛ (አማርኛ)? ደራሲው ምንባቡን በመጀመሪያው ቋንቋ የሚያውቅና እውቀቱንም ለሚሰጣቸው አስተያየቶች የሚጠቀም እስከሆነ ድረስ፥ የማብራሪያው በትርጉም ላይ መመሥረት ክፋት የለውም። ነገር ግን በዕርዕ ወይም የዕብራይስጥ ቋንቋዎች ላይ የተመሠረቱትን ማብራሪያዎች ልትጠቀም እንደምትችልም አስተውል። አንዳንድ ጊዜ የዕርዑ ወይም ዕብራይስጡ ምንባብ አሳብ በደንብ ላይገባህ ቢችልም፥ በአብዛኛው በአነስተኛ ኪሳራ ብቻ ልትወጣው ትችላለህ።

ቀጣዩ መመዘኛ እጅግ አስፈላጊና ግምገማህን ለመጀመር ትክክለኛ ስፍራ ነው።

3. አንድ ምንባብ ከአንድ በላይ አማራጭ ፍችዎች ሲኖሩት፥ የማብራሪያው ደራሲ ሁሉንም አማራጭ ፍችዎች በሚገባ በመዳሰስ፥ በመገምገምና ትክክለኛ ነው ብሎ ለመረጠው አሳብ በቂ ምክንያት በመስጠት ተግባሩን ይወጣል? ለምሳሌ፥ በምዕራፍ 2 ቢያንስ ሦስት አማራጭ ፍችዎች ያሉትን 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡36 ምንባብ በምሳሌነት ተጠቅመናል። ደራሲው ሦስቱንም አማራጮች ካላብራራ፥ እያንዳንዱን የሚደግፉና የሚቃወሙ ምክንያቶች ካልሰጠና የራሱን ምርጫ ካላስረዳ የማብራሪያ መጽሐፉ ሙሉ መረጃ ሊሰጥህ አይችልም።

የሚያስፈልግህን እገዛ በሚገባ ማግኘት ካለብህ የሚከተሉት አራት መመዘኛዎች ጠቃሚዎች ናቸው።

4. ደራሲው የምንባቦቹን ዋንኛ ችግሮች ያብራራል ወይ? ይህንን በምዕራፍ 2 ተመልክተናል።

5. ደራሲው ስለ ምንባቡ አሳብ ታሪካዊ ዳራ በአስፈላጊ ቦታዎች ላይ ያብራራል ወይ?

6. ከፈለግህ ተጨማሪ ጥናቶችን እንድታካሄድ፥ ደራሲው የዋቢ መጻሕፍትን መረጃ ይሰጣል ወይ?

7. በማብራሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው መግቢያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማብራሪያ የምትፈልግለት መጽሐፍ እንዲጻፍ ወሳኝ የነበረውን ሁኔታ እንድትገነዘብ በቂ ታሪካዊ ዓውድ ይሰጥሃል ወይ?

ይህንን ሁሉ ለማድረግ ከሁሉም የሚሻለው መንገድ ከአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድ አስቸጋሪ ጥቅስ መርጦ የማብራሪያ

መጽሐፉ በቂ መረጃ በመስጠት፥ ጥያቄዎችን በመመለስና በተለይም ሁሉንም አማራጭ ፍችዎች በማብራራቱ ረገድ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ ላይ የተጻፈን የማብራሪያ መጽሐፍ ጠቀሜታ ለመገንዘብ ለ11፡10 ወይም ለ7፡36 የሚሰጠውን ማብራሪያ መመልከት ይቻላል። ለመጋቢያን መልእክቶች 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15ን በመፈተኛነት ልትጠቀም ትችላለህ። ለዘፍጥረት 2፡17፥ ለኢሳይያስ 7፡14-17፥ ወዘተ... በመፈተኛነት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

የመጨረሻው ብያኔ የሚሆነው ደራሲው ምንባቡን በዓውዱ በመገንዘብ መረጃውን እንዴት ጥሩ አድርጎ እንደሚያስቀምጥ መመልከት ይሆናል። የታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ምንጭ የሆኑ አንዳንድ ማብራሪያዎች የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መጽሐፍ ደራሲውን ፍች በዓውዱ አያብራሩም።

ጥሩዎች ናቸው ያልናቸውን የማብራሪያ መጻሕፍት ከመዘርዘራችን በፊት ይህንን ነጥብ ደግመን ለማስገንዘብ እንፈልጋለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህን የምትጀምረው በማብራሪያ መጽሐፍ አይደለም! ወደ ማብራሪያ መጽሐፍ የምትሄደው የራስህን ድርሻ ከተወጣህ በኋላ ይሆናል። የማብራሪያ መጽሐፍ የምታነበው በጥናትህ ወቅት በአእምሮህ የተነሡትን የይዘት ጥያቄዎች ለመመለስ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ የማብራሪያ መጽሐፉ ልትጠይቃቸው የሚገቡህ ሆነው ሳሉ ያላስተዋልሃቸውን ጥያቄዎች እንድታነሣ ይረዱሃል።

ከዚህ በታች የምንዘረዝራቸው የማብራሪያ መጻሕፍት ሥነ መለኮታዊ አመለካከታችንን የሚደግፉ አለመሆናቸውን ተገንዘብልን። እንድትመለከት የምንፈልገውም ድምዳሜአቸውን ሳይሆን ከላይ ላነሣናቸው ዓይነት ጥያቄዎች የሚያቋርቧቸውን ማብራሪያዎች ነው። በጥንቃቄና በማስተዋል ተጠቀምባቸው። የዘረዘርናቸው በወንጌል አማኝ ምሁራን የተጻፉ ማብራሪያዎች ሲሆኑ፥ ከፍተኛ ሐቲታዊ አገልግሎት ያበረክቱልሃል ብለን እናምናለን።

## የብሉይ ኪዳን ማብራሪያዎች

በአሁኑ ጊዜ ከላይ የዘረዘርናቸውን መመዘኛዎች የሚያሟላና ወንጌል አማኝ ሥነ መለኮታዊ አመለካከት ያለው ማብራሪያ (1) The Expositor's Bible Commentary የተሰኘው ሲሆን፥ ከእነዚህም መካከል ሁለቱን ተከታታይ ማብራሪያዎች ብታነባቸው መልካም ነው። (2) The New International Commentary (NICOT) (3) The Tyndale Old Testament Commentaries (TOTC). ሌላው

የማብራሪያዎች ተከታታይ እትም «The Word Biblical Commentary» የሚሰኝ ሲሆን፥ የወንጌል አማኝ የሆኑና ያልሆኑ ማብራሪያዎች አሉት። ምናልባትም ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ምርጥ የማብራሪያ መጻሕፍት ምእተ ዓመት ያስቆጠሩት የ«Keil and Delitzsch» ማብራሪያዎች ይሆናሉ። በተጨማሪም አንዳንድ ባለ አንድ ቅጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች ለማንኛውም ቤተ መጻሕፍት እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው፤ እነርሱም “New Bible Commentary Revised (1979), the International Bible Commentary (1979), the Evangelical Commentary on the Bible (1989)” እና የመሳሰሉት ናቸው።


ዘፍጥረት፡ Gordon Wenham. Genesis 1-15 (WBC). Dallas: Word Books, 1987. Joyce Baldwin. *The Message of Genesis* 12-50 (The Bible Speaks Today). Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1988.

ዘጸአት፡ Walter Kaiser, Jr. Exodus (EBC). Grand Rapids: Zondervan, 1979.

ዘሌዋውያን፡ Gordon Wenham. *The Book of Leviticus*. (NICOT). Grand Rapids: Eerdmans, 1979.

ዘኍልቍ፡ Gordon Wenham. Numbers (NOTC). Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1982.

ዘዳግም፡ Peter C. Craigie. *The Book of Deutronomy* (NICOT). Grand Rapids, Eerdmans, 1976.

ኢያሱ፡ Marten Woudstra. *The Book of Joshua* (NICOT). Grand Rapids: Eerdmans, 1981.

መሳፍንት፡ Arthur Cundall and Leon Morris. *Judges and Ruth* (TOTC). Grand Rapids, Eerdmans, 1968.

ሩት፡ Robert L. Hubbard, Jr. The Book of Ruth (NICOT). Grand Rapids: Eerdmans, 1990.

1ኛና 2ኛ ሳሙኤል፡ Joyce Baldwin. *1 and 2 Samuel* (TOTC). Downers Grove Ill.: InterVarsity Press, 1988.

**1ኛ እና 2ኛ ነገሥት፡** Carl F. Keil. *Biblical Commentary on the Books of the Kings.* Edinburgh: T & T Clark, 1876, reprint, Grand Rapids: Eerdmans, 1970.

**1ኛ ዜና፡** J. Barton Payne. *1 and 2 Chronicles* (EBC). Grand Rapids: Zondervan, 1988.

**2ኛ ዜና፡** Raymond Dillard. *2 Chronicles* (WBC). Dallas: Word Books, 1987.

**ዕዝራና ነህምያ፡** Edwin Yamauchi. *Ezra and Nehemiah* (EBC). Grand Rapids: Zondervan, 1988.

**አስቴር፡** Joyce Baldwin. *Esther* (TOTC). Downers Grove, Ill.: InterVarrsity Press, 1984.

**ኢዮብ፡** Elmer Smick. *Job* (EBC). Grand Rapids: Zondervan, 1988.

**መዝሙረ ዳዊት፡** Peter Craigie. *Psalms 1-50* (WBC). Dallas: Word Books, 1983. Derek Kidner. *Paslms 1-72; Paslms 73-150* (TOTC). Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1973, 1975.

**ምሳሌ፡** Derek Kidner. *The Proverbs* (TOTC). Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1964.

**መክብብ፡** Derek Kidner. *The Message of Ecclesiastes* (The Bible Speaks Today). Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1988.

**መኃልየ መኃልይ፡** G. Lloyd Carr. *The Song of Solomon* (TOTC). Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1984.

**ኢሳይያስ፡** John Oswalt, *The Book of Isaiah, Chapters 1-39* (NICOT). Grand Rapids: Eerdmans, 1981. E. J. Young. *The Book of Isaiah. 3 vols.* (NICOT). Grand Rapids: Eerdmans, 1965-72.

**ኤርምያስ፡** John A. Thompson. *The Book of Jeremiah* (Anchor Bible). Grand Rapids: Eerdmans, 1980.

**ሰቆቃወ ኤርምያስ፡** Delbert R. Hillers. *Lamentations* (Anchor Bible). New York: Doubleday, 1972.

**1ኛ ቆሮንቶስ፡** Gordon D. Fee. *The First Epistle to the Corinthians* (New International Commentray). Grand Rapids: Eerdmans, 1987.

**2ኛ ቆሮንቶስ፡** Victor P. Furnish. *II Corinthians* (Anchor BIble). Garden City, N.Y.: Doubleday, 1984.

**ገላትያ፡** Ronald Y.K. Fung. *The Epistle to the Galatians* (New International Commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1988; *Richard N. Longenecker (WBC). Dallas: Word Books, 1990.

**ኤፌሶን፡** F.F.Bruce, *The Epistles to the Colossians, to Philemon, and to the Ephesians* (New International commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1984; Andrew T.Lincoln, *Ephesians* (WBC). Dallas: Word Books, 1990.

**ፊልጵስዩስ፡** Moises Silva, *Philppians*. Chicago: Moody Press, 1988; *Peter T. O'Brien, *Commentary on Phlippians* (New International Greek Testament Commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1991.

**ቆላስይስ፡** F.F. Bruce, *The Epistles to the Colossians, to Philemon and to the Ephesians* (New International Commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1984; *Peter T. O'Brien, *Colossians, Philemon* (WBC). Dallas: Word Books, 1982.

**ተሰሎንቄ፡** Howard Marshall *1 and 2 Thessalonians* (New Century Bible). Grand Rapids: Eerdmans, 1983.

**ጢሞቴዎስ፡** Gordon D. Fee. *1 and 2 Timothy, Titus* (New International Biblical Commentary). Peabody, Mass.: Hendrickson, 1988.

**ዕብራውያን፡** F.F. Bruce, *The Epistle to the Hebrews* (New International Commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1990; William L. Lane, *Hebrews* (WBC), 2 vols. Dallas: Word Books, 1991.

**ያዕቆብ፡** Peter H. Davids, *James* (New International Biblical Commentary). Peabody. Mass.: Hendrickson, 1989; Ralph P. Martin, *James* (WBC). Dallas: Word Books, 1988.

**1ኛ ጴጥሮስ፡** *Peter H. Davids, *The First Epistle of Peter* (Grand Rapids: Eerdmans, 1990; J. Ramsey Michaels, *I Peter* (WBC). Dallas: Word Books, 1988.

**2ኛ ጴጥሮስ፡** J.N.D. Kelly, *A Commentary on the Epistle of Peter and of Jude* (Harper's New Testament Commentaries). New York: Harper & Row, 1969; *Richard J. Bauckham, *Jude, 2 Peter* (WBC). Dallas: Word Books, 1983.

**1ኛ፥ 2ኛ፥ 3ኛ ዮሐንስ፡** *I. Howard Marshall, *The Epistles of John* (New International Commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1978; Stephen S. Smalley, *1, 2, 3 John* (WBC). Dallas: Word Books, 1984.

**ይሁዳ፡ በ2ኛ ጴጥሮስ ሥር ይመልከቱ።**

**ዮሐንስ ራእይ፡** G. R. Beasley-Murray. *The Book of Revelation* (New Century Bible). London: Oliphants, 1974. Robert H. Mounce. *The Book of Revelation* (New International Commentary). Grand Rapids: Eerdmans, 1977.